# መሰማትን ሰምቼ ነበር
# አሁን ግን አየሁ

ተቀመጡ። ዛሬ ማታ እንደገና ተመልሰን መምጣታችን መልካም ነገር ነው። አሁን ጌታን ለማገልገል ዳግመኛ ይህን ዕድል በማግኘታችን ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው። ትናንት ማታ ለረጅም ሰዓት ካቆየኋችሁ በኋላ፡ ዛሬ ማታም እንዲሁ ለረጅም ሰዓት ማቆየት ተገቢ ነው ብዬ አላሰብም።

2 እዚያ ከኋላ ሆኜ ከኢንዲያና የመጣውንና፡ በጌታ አብርን የሚያገለግለውን ወንድማችንን ሰስማው ነበር፡ እሱም እንግዳ በሆነ ሕልም፡ ተረብሾ ነበር። በሕይወቱ፡ ከዚህ በፊት ሽሪቭፖርት መጥቶ አያውቅም። ነገር ግን በቀደም ሌሊት፡ ወደ ሽሪቭፖርት እንደመጣ፡ በህልሙ አየ፡ በመኪናው አይደለም። እንዲሁም ከ... ወይም የሆነ ቦታ መጥቶ፡ እሰብክበት ወደነበረው ቤተክርስቲያን እንደመጣ አየ። እንዲህም አለ፡ ለሕዝቡ ከሰበክሁና ከጸለይኩ በኋላ፡ "'አንድ ነገር ሊፈጠር ነው፡'" አልክ አለኝ። እንዲህም አለ፡ "በማግስቱ ተመልሼ ነበር።" እንዲሁም፡ "ሕንጻውን፡ ምን እንደሚመስል አውቄ ነበር" አለ። እንዲህም አለ፡ "ከ—ከመንገዱ ማዶ የ—የህዝብ አዳራሽ ነበረ፡ ሆኖም ግን ወደ አዳራሹ በፍጹም አልገቡም።" እንዲህም አለ፡ "በዚህኛው በኩል፡ ክንፍ ባለው የድንጋይ ሕንጻ ውስጥ ነበር፡ ሕንጻውም ልክ እንደዚህኛው ነበር።" ልጁም ሕልም አላሚ ነው፡ ሕልሞቹን አይቻለሁ እውነት መሆናቸውንም አውቃለሁ።

3 እንዲህም አለ—እንዲህም አለ፡ "ከዚያም በመጨረሻው ምሽት" እኔ "የታመሙትን እያነጋገርኩ ስጸልይላቸው" ነበር። እንዲህም አልኩ፡ "'አንድ ነገር ሊሆን ነው፡' ልክ እንደ ነጎድጓድ ድምፅ ይሰማ ነበር።" ከዚያም፡ "ሕዝቡም መጮህ ጀመሩ" አለ። አለም፡ "ነጎድጓዱ እየራቀ በሄደ ቁጥር፡ እንግዲህ፡" እንዲህ አለ "ወደ ድምፅነት ተቀይሮ፡ መናገር ጀመረ።" እንዲህ ይላል፡ "ያ ንግግር እየቀጠለ ሳለ፡ በእነዚህ ፍርግርጎች በኩል (ከላይ ባሉት መስኮቶች) የእግዚአብሔር ክብር፡ በእሳት ዓምድ መልክ፡ ገባ።" ከዚህ በፊት አይቶት አያውቅም። ስለሱ ስንነጋገር ሰምቷል፡ ነገር ግን እሱ ራሱ አይቶት አያውቅም። እንዲህም አለ፡ "እንዲህ ሆነ፡ በዚያ መልኩ ከላይ በመስኮቶች በኩል ገብቶ፡ ልክ በሥዕሉ ላይ እንደምታዩት፡ በዚህ በጉባኤው ላይ ብርሃን ሠራ።" እንዲህም አለ፡ "የሆነ ዓይነት ማንጓጓት ነበር።" አለም፡ ከዚያ እኔ "እዚያ ቆሜ፡ 'ያ ይሖዋ አምላክ ነው'፡" አልኩ።

4 እንዲህም አለ እርሱ "ይህን (ስለሱ ሲያስብ ሳለ) ሙሴ ሕዝቡን... ከግብፅ ያወጣበት ጊዜ ትዝ አለው። ከዚያም እነርሱ፡ 'እንዳንሞት፡ እግዚአብሔር አይናገረን፡ አንተው ሙሴ ተናገረን' አሉ" አለ።

5 "ሁሉም ወለሉ ላይ ወድቀው፡ እጆቻቸውን ወደ ላይ አንስተው፡ ይጮሁ ነበር፡" አለ። እሱም ራሱ፡ "'ጌታ አምላክ ሆይ፡ እወድሃለሁ! እወድሃለሁ!' እያልኩ እጮህ ነበር" አለ። ከዚያም ሚስቱም ነቅንቃ ቀሰቀሰችው።

6 ይኸውላችሁ የቀድሞ የሜቶዲስት ሰባኪ የነበረው፡ ወንድም ጃክሰን፡ በመተላለፊያው ሲሄድ ተመልከቱት። እስኪወርድ ድረስ፡ በጣም ተረብሾ እንደነበር፥ ውስጥ ሲገባ፡ “በጣም ተደነቅኩኝ” ብሏል፡ ይህም ልክ በሕልም እንዳየው ነው። ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። ጌታ ከእኔ ሰውሮታል። ሆኖም ወንድም ጃክሰን እንዲህ አይነቱ ሕልም ማየቱ፡ የሆነ ነገር መከሰቱ አይቀሬ ነው፡ ት—ትክክለኛ ሰው፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን፡ እናውቃለንና።

7 እኔም እ—እሱ ሕልሞችን አልሞ፡ ወደ እኔ ሲመጣ፡ ጌታም ትርጓሜውን ይሰጠኝ እንደነበር፡ በትክክል እንደዚያው ይሆን እንደነበርም አውቃለሁ። አንድ ጊዜ፡ ወደ አሪዞና ያደረግኩት ጉዞ፡ ሳይቀር፡ በሕልሙ አይቶት ነበር።

8 በጣምም ተረብሿል። ከሚስቱ ጋር ነው፡ እሷንም አምጥቷታል። በቅርቡ እናት ልትሆን ነው፡ ሊመጣ የሚችልበት ብቸኛው መንገድም በአውሮፕላን ነበር። ለመምጣት አንድም ሳንቲም አልነበረውም፡ ሆኖም አንድ ሰው ገንዘብ ሰጠው። በመሆኑም በምስጢራዊ ሁኔታ ሊሳካ ችሏል፡ ስለዚህ የሆነ ነገር ሊከሰት ይችላል፥ ተሰፋ እናደርጋለን። ጌታ ምን እንደሚያዘጋጅልን በትክክል አናውቅም።

9 አሁን፡ የኢየሱስ መምጣት በተቃረበበት፡ በምንኖርበት በዚህ ዘመን በመኖራችን ጌታን እናመሰግናለን። ከዚህ በፊት እንዳልኩት፡ በታሪክ ሁሉ ታላቁ ጊዜ ነው። ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ፡ በ... በምድር ላይ አሁን መኖሬን እመርጣለሁ።

10 ሌላ ደግሞ ዛሬ ማታም፡ እዚህ ከፊታችን፡ ጥሩ ጓደኛዬ፡ ወንድም ዳውችን ይታየኛል። ዛሬ ጠዋት በአዳራሹ ውስጥ አነሰቼው ነበር። ወንድም ዳውች ዛሬ የዘጠና-ሦስት ዓመት አዛውንት ሆኗል፡ ምንኛ የተባረከ ነው። ረጅም ዕድሜውን ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና አበርክቷል፡ ዛሬ ዘጠና-ሦስት ሆነው። ወንድሜ፡ “መልካም ልደት” ይሁንልህ! ዛሬ ማታም፡ በየሰፍራው፡ በመላው ሀገሪቱ አድማጮች በያሉበት ሁሉ፡ ለወንድም ቢል ዳውች “መልካም ልደት” እንደሚመኙለት አውቃለሁ። የኦራል ሮበርትስ በጣም የቅርብ ጓደኛ ነው፡ ብዙዎችን፡ በወንጌል ጎዳና ውስጥ ብዙዎችን ረድቷል፡ በሁሉም ነገር። ታላቅ ጓደኛችን ነው።

11 ሌላው የሜቶዲስት ሰባኪ፡ የዳነና በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ፡ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም የተጠመቀ፡ ወንድም ማን፡ እዚህ ተቀምጦ ማየቴ ደስ ብሎኛል። እሱም፡ እንዲሁ፡ ከኢንዲያና ከመጡት አጋሮቻችን አንዱ ነው። ከጀፈርሰንቪል ኢንዲያና ዲያቆኖቻችን አንዱ የሆነው፡ ከጀፈርሰንቪል ኢንዲያና ከሆኑት ዲያቆናቶቻችን አንዱ፡ ወንድም ሂከርሰን በአጠገቡ እንደተቀመጠ ተረድቻለሁ (እዚያም ዛሬ ማታ እያዳመጡን ነው)። ሌላው ከዲያቆናቱ አንዱ የሆነው ወንድም ዊለርም፡ እዚህ የሆነ ቦታ እንዳለ ተረድቻለሁ። እ—እስካሁን የት እንዳለ አላየሁትም፡ አንድ ሰው በጣቱ እየጠቆመ ነው ከትንሽ ጊዜ በኋላም አገኘዋለሁ፥ እዚያ ላይ ተቀምጧል፡ ወደ ቀኝ በኩል ራቅ ብሎ፡ አዎን።

ወንድም ባንክስ ውድ፡ ዛሬ ማታ እያዳመጥክ ከሆነ፡ ወንድምህ ትናንት ማታ እዚህ ነበር። እኔ ሰወጣ አይቼዋለሁ፡ ወንድም ላይል። የይሖዋ ምሥክር፥ መላው ቤተሰብ ተለውጧል። ላይል የመጣው በጌታ ራእይ ምክንያት ነበር።

12 በዚያን ዕለት ላይል በታንኳው ላይ ተቀምጦ፡ ያን ቀን "የአንድ ፍጡር ከሞት መነሣት አስመልክቶ" "የሆነ ነገር ይከሰታል" ተብሎ ተነግሮት ነበር። እሱም፡ እውነተኛ የይሖዋ ምስክር ነበር! ነገር ግን በዚያ ጠዋት፡ እዚያ ተቀምጦ፡ ዓሣ እያጠመደ ሳለ፡ አንዳች ነገር ሆነ... እንግዲህ፡ ትልቅ፡ (የኬንታኪ አይነት፡ ታውቃላችሁ)... ትልቅ መንጠቆ ይዞ ነበር፡ ትንሽዬው ዓሣ ዋጠው። እሱም ጉሮሮውን፡ አንጀቱንና ሁሉንም ነገር አውጥቶ፡ ውኃው ላይ ወረወረው (በጣም ትንሽ፡ ሰንፊሽ የሚባል ዓሳ ነበር)፡ እንዲህም አለ፡ "እንግዲህ፡ አንተ ትንሽ ዓሳ፡ የመጨረሻ ጥይትህን ተኩሰሃል።" ትንሹ... ውኃው ላይ እየተንቀሳቀሰ፡ ሞተ፡ ነፋሱም ገፍቶ ወስዶ ከኩሬ አበቦች ውስጥ ጨመረው።

13 ከአንድ ቀን በፊት፡ ቁጭ ብዬ፡ እንዲህ አልኩ፡ "መንፈስ ቅዱስ 'የሆነ የአንድ ትንሽ ፍጡር ትንሣኤ ይኖራል' ይለኛል። ቤት ስመለስ፡ ምናልባት አ—እንዲት ትንሽ ድመት ትሆን ይሆናል፡ ምክንያቱም... "

14 እኔ እና ወንድም ውድ፡ ለዓሣ ማጥመጃ የሚሆነንን ቆፍረን እያወጣን ሳለ፡ እርሱ አሁን እያዳመጠ ነው፡ እዚህ ተቀምጣ ያለችው ወጣቷ ልጄ፡ ከዚህ መለሎ ወታደር ጋር ታጭታለች። እነሱ... እሷ መጣችና፡ "አባዬ፡" አለች... እሷና ሌላኛዋ ትንሽ ልጅ፡ እንዲህ አሉ፡ "እኛ... " እንግዲህ፡ ማንኛውም ሰው የፈለገውን ዓይነት የቤት እንስሳ ሊያሳድግ ይችላል፡ ድመትን ግን በእርግጠኝነት አልወድም፡ እ... ወይም ማናቸውም የብራንሃም ቤተሰብ አይወዱም። ስለዚህ እ... እንዲህ አለች፡ "ኦህ፡ እዚህ ውጪ አንዲት ምስኪን ድመት አገኘን፡ አባዬ። የ—የ—የሆነ ነገር በልታለችና... የሆነ ሰውም መርዝ አብልቷታል፡ በሙሉ አብጣለች።" እንዲህም አለች፡ "አባዬ፡ አሁኑኑ ትሞታለች፡ ትንሽ ካርቶን አምጥተን ለሁለት ቀናት እናቆያት ወይ? "

15 እኔም "ድመቷን ልያት፡" አልኳቸው። መልካም፡ ሄደው ድመቷን አመጧት። ምን ሊፈጠር እንደሚችል ስለተረዳሁ፡ ካርቶን ሰጧኋቸው። በማግስቱ ጠዋት፡ ወደ ሰባት ወይም ስምንት ግልገሎች ነበሩ፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህ ትንሹ ልጄ፡ ጆ፡ አንዱን አንስቶ፡ ጨመቀውና መሬት ላይ ጣለው፥ እና እ—እ... ትንሹ ፍጡር እዚያ ወድቆ እየተንቀሳቀሰ ቆየና፡ ገደለው።

16 እኔም ወንድሙ፡ ለወንድም ላይል እንዲህ አልኩት፡ እንዲህ አልኩት፡ "ታውቃለህ፡ ጌታ ነገሮችን ሲያደርግ እንዳየነው፡ ያቺ ትንሽ የድመት ግልገል ተነስታ ሊሆን ይችላል።"

17 ወንድም ላይል፡ ለመንገዱ አዲስ ነበር። እርሱ ያገባ መሆኑን የሰራቸውን ክፋቶች፡ ምን እና ምን እንዳደረገ፡ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ መንፈስ ቅዱስ ተናግሮት ነበር። እንግዲህ፡ እነዚያን ነገሮች ወንድም ባንክስ ነግሮት ነው ብሎ አስቦ ነበር። ከትናንት ማታ በፊት ያደረጋቸውን ነገሮች፡ አውጥቶ ሲነግረው ግን፡ ያ—ያ ለእሱ በጣም ከባድ ነበር። ሊረዳው አልቻለም።

18 ከዚያም፡ በማግስቱ ጠዋት... ትንሹ ዓሣ፡ ሌሊቱን ሙሉ ዓሣ ስናጠምድ ቆይተን፡ የተወሰኑትን ለማጥመጃነት እየያዝን ነበር። ነገር ግን ትንሹ ዓሣ ወደ ውኃ ውስጥ ወረወረው፡ ተንቀጠቀጠ፡ ተንፈራገጠ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ እዚያ ተቀምጠን ነበር፡ እናም እ... እንዲህ አልኩት፡ "ወንድም ላይል፡ ዓሣው መንጠቆውን እስከ ሆዱ ድረስ እንዲውጠው አደረግከው። አየህ? " እንዲህ አልኩ፡ "ይህን ማጥመጃ ክር እዚህ ጋር ያዘው፡ ወደ ውጭ ወርውረው፡

ማጥመጃውም እንደዚህ ይውጣ፥ ልክ እንደነካው፡" እንዲህ አልኩት "ከዚያም ያዘውና ወደ ውስጥ አስገባው።" እንዲህ አልኩት፡ "እ... እንደዚህ አትጎትተው፡ አይዋጠው፡ ዓሣውን አጥምደው።"

19 እሱም አለ፡ "እንግዲህ... " ትልቅ፡ ማጥመጃ ገመድ ይዞ ነበር፡ እንዲህም አለ፡ "እኛ የምናደርገው በዚህ መንገድ ነው፡" እንዲህ አደረገ።

20 እናም፡ ያን ጊዜ፡ ከላይ ከተራራው ጫፍ አንድ ነገር ሲመጣ ተሰማኝ፡ አውሎ ነፋስ፡ እየተሸከረከረና እየተሸከረከረ። እንዲህ እያለ ወረደ፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በጀልባዋ ላይ መጥቶ፡ "በእግርህ ቁም፡" አለኝ። እንዲህም አለኝ፡ "ለሞተው ዓሣ ተናገረው። 'ሕይወትህን መልሼ ሰጠሁህ' በለው፡" አለኝ።

21 ትንሹ ዓሣ አንጀቱና ጉሮሮው አፉ ላይ ሆኖ፡ ለግማሽ ሰዓት ያህል፡ እዚያው ተጋድሞ ነበር። እንዲህም አልኩ፡ "አንተ ትንሽ ዓሣ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትህን መልሶ ሰጥቶሃል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በሕይወት ኑር" አልኩት። በጀርባው ተገለበጠና፡ በሚችለው ፍጥነት ወደ ውኃው ውስጥ ጠልቆ ገባ።

22 ወንድም ላይል፡ እዚህ ነህ የት ነህ? ት—ትናንት ማታ አይቼሃለሁ። ውስጥ ይሁን፡ ውጪ፡ ወይም ባለበት ቦታ ሆኖ፡ ላየው ከቻልኩ እጁን ያንሳ። [አንድ ሰው፡ "በረንዳ ላይ" አለ።—አርታዒ።] ምን አልክ? በረ-... ኦህ፡ አዎ፡ እዚያ ጀርባ ባሉት መስኮቶች በኩል፡ እዚያ ላይ በረንዳው ላይ። ሰውዬው ያ ነው፡ የይሖዋ ምስክር።

23 እሱም፡ "ወንድም ብራንሃም" አለ! በጣም ተገርሞ፡ እንዲህም አለ፡ "ኧሃ፡ እ—እዚህ መሆን መልካም ነው። አይደል እንዴ? " እንዲህም አለ፡ "ኧ-ሃ፡ አንተ—አንተ... ኧህ፡ ያ ማለት እኔን ማለትህ ይመስልሃል፡ ያ—ያ—ያ፡ ያንን ትንሹን ዓሣ፡ 'የመጨረሻ ጥይትህን ተኩሰሃል፡' ያልኩትን? " እንዲህም አለ፡ "ያ—ያ—ያ ለእኔ የሆነ ትርጉም ነበረውን? "

24 እኔም፡ "አይ፡ አይ፡ ማረጋገጫ ብቻ ነው" አልኩት። ስለዚህ ጉዳይ በጣም ተረብሾ ነበር።

25 እንግዲህ፡ አብረን ስንጓዝ እነዚያ ነገሮች ሲከሰቱ ታያላችሁ፡ እንድታውቁት... እሰቲ፡ አስቡት፡ ያ ምንን ለማሳየት ነበር? በጸሎት ዝርዝሬ ላይ ብዙ ሽባ-ህጻናት ነበሩ፡ ስጸልይላቸውም ነበር፡ ነገር ግን ራእዩ ሲመጣ ሁለት ወይም ሦስት ኢንች ያህል ርዝመት ላላት፡ አንዲት ትንሽ ዓሣ ነበር። መንጠቆ ልክ እንደ ዓሣዋ ትልቅ ይመስል ነበር። ነገር ግን ያ የሆነው፡ እግዚአብሔር ለትንንሽ ነገሮችም ጭምር ትኩረት እንደሚሰጥ ሊያሳያችሁ ነው። አያችሁ?

26 በአንድ ወቅት በሀገሪቱ ሁሉ ለምጻሞች ተኻተው በነበረበት ጊዜ፡ ኃይሉን ተጠቅሞ አንድን ዛፍ ረገመ። ያንን የፈውስ ኃይል የሚፈልጉ ሰዎች በየቦታው ተኻተው ሳለ፡ ዛፉ መድረቅ ጀመረ። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ትንሽም ይሁን፡ ትልቅም ይሁን፡ ምንም ይሁን ምን፡ በሁሉም ነገር ላይ አምላክ መሆኑን ሊያሳይ ፈልጎ ነበር። እሱ አሁንም በነገሮች ሁሉ ላይ፡ በፍጥረት ሁሉ ላይ አምላክ ነው። ስለዚህ እንወደዋለን ምክንያቱም... ያ—ያ የሚያሳውቀን፡ በውኃው ላይ ለግማሽ ሰዓት ሞቶ ለተኛው አንድ ትንሽ ግምት ለማይሰጠው ዓሣ የሕይወትን ቃል ለመናገር ትኩረት ከሰጠ፡ አንድ ቀን ያለጥርጥር፡ ለልጆቹ ሕይወትን መናገር ይችላል። ሰውነታችሁ ከአንድ ማንኪያ አፈር የማይበልጥ ቢሆንም

እንኳ፡ እሱ ይናገራል፡ እኛም አንድ ቀን እንመልስለታለን። በምናደርገው ሁሉ፡ በምንናገረው ሁሉ፡ በሁሉም ነገር ላይ፡ ትኩረት የሚያደርግ አምላክ ነው። እሱ ትኩረት ይሰጣል።

አሁን በሁሉም ቦታ፡ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

27 አሁን ከመጸለያችን በፊት፡ ዛሬ ማታ፡ በእሱ ላይ ፍላጎት ያለው፡ ዳሩ ግን እሱን ልናይ ባለንበት በዚያኛው ሀገር ገና ቦታ ያላሰያዘ ሰው ካለ እጠይቃለሁ። ታውቃላችሁ፡ ቦታ ሳታስይዙ መግባት አትችሉም። ገና ያላስያዛችሁ፡ ነገር ግን አሁን በጸሎት መታሰብ የምትፈልጉ፡ ዛሬ ማታ በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል ሁሉም ነገር ትክክል እንዲሆን የምትፈልጉ፡ እጃችሁን ብቻ በማንሳት፥ “ጌታ ሆይ፡ አስበኝ፡” ትላላችሁን? እናንተ... እጃችሁን እንዲያይ ፍቀዱለት። እግዚአብሔር ሆይ፡ ይሁንልን።

28 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ በሕያዋንና በሙታን መካከል ቆመን ሳለ፥ በእነዚህ ቀናት እየተከሰቱ ያሉ እነዚህ ነገሮች፡ ምስጢራዊ ናቸው፡ በእርግጥ ምስጢራዊ ናቸው፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ሆይ፡ እውነት መሆን አለመሆናቸውን አንተ ታውቃለህ፡ አንተ የሰማይና የምድር ጻድቅ ፈራጅ ነህ። ጌታ ሆይ፡ ይህን የምንለው፡ ሰዎችን ለማበረታታት ብቻ ነው (ካሳየኸን ነገሮች አንዳንዶቹን)፡ አንተን እንዲወዱና እንዲያምኑብህ፡ እንዲያገለግሉህ፡ እንዲሁም የሚያደርጉት ነገር ምንም ያህል ትንሽ ቢሆን፡ ጥሩም ሆነ መጥፎ፡ አንተ እንደምታየው እንዲያውቁ በማሰብ እንዲበረታቱ ነው። ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ማታ እነዚያን እጆች እያንዳንዳቸውን፡ ያም እጅ ወደ ላይ እንዲነሳ ያነሳሳውን ነፍስና መንፈስ እንድትባርክ እጸልያለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ከወንዙ ማዶ ላለችው ለዚያች ሀገር ቦታ የሚያሰይዙበት ምሽት እንዲሆን እጸልያለሁ። ይሁንልን።

29 ጌታ ሆይ፡ የታመሙትን እና የተጨነቁትን ፈውሳቸው፡ እዚህ ያሉትን፡ በምድሪቱ ሁሉ በሰልክ መስመር ሰ—ሰ—ሰርጭት የሚከታተሉትን ሁሉ ይፈወሱ። ከካሊፎርኒያ እስከ ኒውዮርክ፡ ከካናዳ እስከ ሜክሲኮ ያሉትን እዚያ ውጪ ያሉትን፡ ያልዳኑትን ባርካቸው። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በድምፃችን ሥር ያለ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በመለኮታዊ ሕልውናህ ምክንያት፡ ከኃጢአቱ እንዲድንና፡ ከበሽታውም እንዲፈወስ አድርግ።

30 ይህ ወንድማችን ጃክሰንም፡ ልቡን የሆነ እንግዳ ነገር ሰላነሳሳው፡ ይህን ሺህ ማይል አቋርጦ በመብረር እዚህ ተገኝቷል፥ “ሕልሞችንም ያልማሉ፡ ራእዮችንም ያያሉ።” ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ከእኔ ምስጢር አድርገህ ሰውረኸዋል፥ አላውቅም። ነገር ግን ጌታ ሆይ፡ የምትጎበኘን ከሆነ፡ ለዚያ ጉብኝት አሁን ልባችንን አዘጋጅልን። ምን እንደምታደርግ ሳናውቅ፡ በዚህም ሕልም ልትጎበኘን ቃል እንደገባህ ሳናውቅ፡ በመጠባበቅ ውስጥ እንድንሆን አዘጋጅልን፥ አናውቅም። ነገር ግን እኛ ሕዝብህን ልትጎበኝ ቃል እንደገባህ፡ የ—የምንረዳቸውን ነገሮች ብቻ እየጠቀስን ነው፡ እራስህንም ለእኛ እውን እንድታደርግልን እንጸልያለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

31 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ትናንት ማታና ዛሬ ጠዋት ለረጅም ሰዓት ካቆየኋችሁ በኋላ፡ ድምፄ ትንሽ እየተያዘ ነው። ስሰብክ **እዚህ** ራሰ በራዬ ላይ የማደርጋት፡

ትንሽ የፀጉር ቁራጭ አለችኝ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ረሳኋት፡ በእነዚህ መስኮቶች በኩል የሚገባው፡ ይህም አየር፡ ት—ትንሽ ድምጼ እንዲዘጋ ማድረግ ጀምሯል። ከዚህ በፊት... ስብሰባዎችን ማቋረጥ ነበረብኝ፡ ነገር ግን ያቺን ካገኘሁ ወዲህ፡ አልጨነቅበትም ነበር፡ ዝም ብዬ እቀጥላለሁ። ረስቻታለሁም፡ ደግሞም... እኔ... ሊሰማኝ ይችላል፡ ስለዚህ ጸሎታችሁ አስፈላጊ ይሆናል። አሁንም፡ እነዚህ በእያንዳንዱ ቀን የሚደረጉ ሁለት አገልግሎቶች ናቸው፡ እነሱም... ምን አልባት... ታውቃላችሁ፡ ብዙ ማይል ስትጓዙ፡ እሱ... ያስታውቃል።

32 ስለዚህ አሁን በካሊፎርኒያ፡ እንዲሁም ውጭ አሪዞና ላላችሁ ሰዎች፡ ሁላችንም በሀገሪቱ ሁሉ ሰላምታ እንልካለን። በፕሬስኮት ጌታን እየጠበቁ ያሉ ወንድም ሊዮና ቡድኑ፡ አሁን ተጋብዘዋል፡ እንዲሁም በፊኒክስ ዙሪያ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ፡ ከዛሬ ማታ ጀምሮ ባለው አንድ ሳምንት ውስጥ፡ ዩማ ውስጥ በድግሱ ላይ እንሆናለን። ትኬቶቻቸውን ሁሉ ሸጠው ጨርሰው ትልቅ የስብሰባ አዳራሽም አግኝተዋል፡ ሆኖም ሰዎቹን ማስተናገድ አልቻሉም። ስለዚህ ሁላችሁም፡ ለ—ለመግባት፡ በጊዜ ኑ። ከዚያም ከዚያ ተነስተን ወደ ሎስ አንጀለስ እንሄዳለን፡ በሚቀጥለው ሰኞ... በሚቀጥለው እሁድ፡ እሁድ ማታ። ስለዚህ ሁላችሁንም እዚያ ለማየት እየጠበቅን ነው። የእግዚአብሔር የበለጸገ በረከት በሁላችሁም ላይ ያርፍ።

33 በኒውዮርክ ላላችሁ፡ እንዲሁም በኦሃዮና በተለያዩ ቦታዎች ዙሪያ ላላችሁ፡ በቅርቡ **የእባቡን መንገድ** የሚል መልእክት መስበክ እፈልጋለሁ (አውሬው በመጀመሪያው፡ እንዲሁም አውሬው በመጨረሻው)፡ በታበርናክሉ ላይ። ለዚህም መቼ እንደምንናገረው፡ ቢሊ ማስታወሻ ይልክላችኋል፡ በታበርናክሉ ውስጥ የማደርግበት ምክንያት፡ ቢያንስ፡ አራት ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ስለሚፈጅ ነው።

34 ስለዚህ አሁን... ስለዚህ እዚህ ያላችሁት፡ እዚህና አሁን ባላችሁበት ቦታ ሁሉ፡ ወደ ኢዮብ መጽሐፍ እንድትገልጡ እፈልጋለሁ። ለመስበክ በጣም እንግዳ የሆነ መጽሐፍ ነው፡ ነገር ግን አሁን እዚህ ጥቂት ማስታወሻዎችን ብቻ መጠቀም እፈልጋለሁ።

35 ከዚያም፡ ነገ ጠዋት፡ እዚህ በታበርናክል ውስጥ፡ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች በ... እዚህ ስንት ሰዓት እንጀምራለን? [አንድ ወንድም፡ "ዘጠኝ-ተኩል" አለ።—አርታዒ።] ዘጠኝ-ተኩል። ከዚያም ነገ እዚህ እንደገና የመናገር ዕድል አለኝ። ጌታ ቢፈቅድ፡ በርዕሱ ላይ ለመናገር ፈልጌ ነበር... እሱ ቢፈቅድ፡ አሁን፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ሳጠና እንደነበረው፡ "እግዚአብሔር መሰዋዕት አቅራቢውን የሚገናኝበት አንድ ቦታ ብቻ አለ፡" የሚለውን ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። ኧ-ህ፡ ብቻ... ያም—ያም ቦታ ምን እንደሆነ፡ እንዲሁም እግዚአብሔር አምልኮ አቅራቢውን የሚገናኝበት፡ የዚያ ቦታ ስሙ ማን እንደሆነ ልነግራችሁ እችላለሁ።

36 ከዚያም፡ ነገ ማታ፡ አንድ ውለታ ልጠይቅ ነው፡ ያም፡ የፈውስ አገልግሎት እንዲሆን ነው። እ—እኔም የጥንቱን-አይነት የፈውስ አገልግሎት እፈልጋለሁ። ጌታ ቢፈቅድ፡ ዛሬ ስላሰደነገጠኝ ርዕስ መናገር እፈልጋለሁ... እኔና ወንድም ሙር አብረን ውጪ እየተነጋገርን ሳለ፡ ውድ ወንድሞቼ፡ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እየተወያየን ነበር። ልክ እንደ ጥንቱ ጊዜያት፡ ከእነዚያ ወንድሞች ጋር መሆን

ምንኛ ደስ ይል ነበር። እሱም እንዲህ አለ፡ “ታውቃለህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እዚህ ሽሪቭፖርት ውስጥ ለእኛ ከሰበክሃቸው ሰብከቶች ሁሉ፡ **በጉና ርግቡ** የሚለው እዚህ ሽሪቭፖርት ውስጥ ካመጣህልን መልእክቶች ሁሉ በጣም አስደናቂው ነበር” አለ። እንዲህም አለ፡ “ዛሬ መልእክትህ በጣም አድካሚ ስለሆነብህ፡ እንደዚያ ዓይነት በፍጹም አትሰብክም ብዬ አስባለሁ።”

37 “ያንን ሳጣ፡ መልእክቴን አጣለሁ።” ፍቅር የእኔ...

ውድ ሟች በግ ሆይ፡ ክቡር ደምህ
ኃይሉን በፍጹም አያጣም፡
የተዋጀችው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሁሉ
ዳግመኛ ኃጢአት እንዳትሰራ፡ ድና።

ያንን ምንጭ ካየው በእምነት
ከሚፈሰው ቁስል የሚወርድ፡
የመቤዠት ፍቅሩ መዝሙሬ ሆኗል፡
እስክሞት ድረስም ይሆናል።

38 ነገ ማታ፡ የጌታ ፈቃድ ከሆነ፡ በአንድ ርዕስ ላይ ልሰብክ እፈልጋለሁ ይኸውም፥ **እንደ በረዶ ነጭ-በሆነች ርግብ ክንፎች ላይ**። ነገ ማታ፡ “ጌታ በርግብ ክንፎች ላይ ሲወርድ፡” ያም፡ ጌታ ቢፈቅድና፡ ድምፄ በጣም ካልተበላሸ ነው። አሁን... ስለዚህ፡ ጸልዩልን።

39 ከዚያም በመጀመሪያ እንደነበረን ያለ የጥንቱ-አይነት የጸሎት ሰብሰባ እፈልጋለሁ፡ ምንም የመለየት መንፈስ ሳይኖር፡ ዝም ብሎ እንዲጸለይለት ለሚፈልግ ሁሉ ካርድ በመስጠት እንዲሆን እፈልጋለሁ። አሁን፡ ካርድ ሊኖራችሁ ይገባል፡ ስለዚህ ቢሊ ካርድ ሰጥቷችሁ በሰልፍ እንዲያቆማችሁ በጊዜ እዚህ ተገኙ። ያንን ካላደረጋችሁ፡ ሰዎች ዝም ብለው ይመለሳሉ፡ ተመልሰውም ይመጣሉ፡ ተመልሰውም ይመጣሉ፡ ሰልፉም መጨረሻ የለውም። ማንም ሰው ካርድ ማግኘት ይችላል። ወንድም ጃክ ከዚህ በፊት ታደርገው እንደነበረው፡ በጸሎት መሰመሩ ላይ ከጎኔ እንዲቆም እፈልጋለሁ፡ እንዲሁም ከቢሊ ፖል ይልቅ ወንድም ብራውን ሰዎቹን ወደ እኔ እንዲያመጣ እፈልጋለሁ። እ—እ—እ—እ የ—የቀደሞው-አይነት የጸሎት መሰመር እፈልጋለሁ፡ ከዓመታት በፊት እንጸልይ እንደነበረውም ዝም ብለን እንጸልያለን።

40 ዛሬ ማታ ሌላ አጋር ወንድም ከእኛ ጋር በመኖሩ ደስ ብሎኛል፡ ዙሪያዬን ስመለከት አወቅሁት፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊትም አየሁት፡ ወንድም ጎርደን ሊንሴይ። ከቀድሞዎቹ አንዱ ነው፡ ከረጅም ጊዜ በፊት ከእኛ ጋር ነበር። በማተሚያ፡ ታላቅ ሥራ እየሠራ ነው፡ መጽሐፌን አሁን እያተመው ነው፥ **ሰ—ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት። ሰባቱ ማኅተሞችን፡** እንደገና አዘጋጅተን ለመጨረስ ተሰፋ እናደርጋለን። ከማተሙ በፊት ያንን የሚያነበው ከሆነ፡ ሥነ መለኮታዊ ውይይት ይኖረናል። ያ እየመጣ እንደሆነ ይሰማኛል። ነገር ግን እኔ የሥነ መለኮት ምሁር እንዳልሆንኩ ያውቃል። ስለዚህ... እንግዲህ፡ ነገ ማታ በጉጉት እየጠበቅን ነው። ወንድም ሊንሴይ፡ እዚህ ካለህ፡ ነገ ማታ እዚህ ተገኝ። ከሆንክ፡ ብቅ በልና በጥንቱ-አይነት የጸሎት ሰብሰባ በመድረኩ ላይ ከእኛ ጋር ሁን።

41 ሰንቶቻችሁ ሰዎቹን ወደ መድረክ የምናመጣበትን፡ ከእነዚያ የቀደምት-ዓይነት ስብሰባዎች አንዱን እንደገና ማየት ትፈልጋላችሁ? ያ ጥሩ ይሆናል። አሁን፡ ለዚያ ዓላማ ሲባል፡ ነገ ማታ፡ የታመሙትንና የተሰቃዩትን እምጧቸው።

42 አሁን፡ የኢዮብን መጽሐፍ ከከፈታችሁ፡ 42ኛውን ቁጥር... ወይም 42ኛውን ምዕራፍ፡ እንዲሁም የኢዮብን 42ኛ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ቁጥሮችን እናያለን፥ በጣም እንግዳ ነው። ወንድም ቴድ ዳድሊ፡ ዛሬ ማታ እዚያ ፊኒክስ ውስጥ እያዳመጥክ ከሆነ፡ እኔና አንተ በአንድ ወቅት፡ ከአንድ ወይም ከሁለት ሳምንት በፊት፡ ስንነጋገር ይህንን ጠቅሰነው እንደነበር፡ ታስታውሳለህ? "አንድ ቀን ይህ ለእኔ መልእክት ይሆናል"፡ ብዬህ ነበር። ዛሬ ማታም ልጠቀምበት እፈልጋለሁ።

**ከዚያም** መለሰ...

**ኢዮብም ለእግዚአብሔር መለሰ፡ እንዲህ አለ፡**

አሁን ይህን ንባብ በጥሞና አዳምጡ።

**ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፡ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።**

**ያለ እውቀት ምክርን የሚሰውር ማን ነው? ስለዚህ እኔ የማላስተውለውን፥ የማላውቀውንም፡ ድንቅ ነገር ተናግሬአለሁ።**

**እባክህ፡ ስማኝ፡ እኔም ልናገር፥ እጠይቅህማለሁ፡ አንተም ተናገረኝ።**

**መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፥ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ።**

**ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፡ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።**

43 አሁን ከዚያ ከ5ኛው ቁጥር ርዕስ ልወስድ እፈልጋለሁ።

**መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ።**

ጌታ ቃሉን ይባርክ።

44 ኢዮብ፡ ከሕይወቱ ጥቂት እንውሰድ፡ ኢዮብ ነቢይ ነበር፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት የኖረ ሰው ነበር። ዘፍጥረት ከመጻፉ በፊት ስለተጻፈ፡ የኢዮብ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ጥንታዊ ከሆኑት መጻሕፍት አንዱ እንደሆነ ይታሰባል። ይህ ታላቅ ተዋጊና ነቢይ የሆነው ኢዮብ፡ በዘመኑ ኃ—ኃያል ሰው ነበር። በሕይወቱ ሙሉ ጌታን እንዳገለገለ እንዲሁም ሕዝቡ ሁሉ ለእርሱ አክብሮት እስከሚኖራቸው ድረስ፡ እንዲህ ያለ የጀግንነት ሕይወት እንደኖረ ምንም ጥርጥር የለውም።

45 ዳሩ ግን እዚህ እንዳለው፡ በጌታ **ወደሚፈተንበት** ደረጃ ደርሶ ነበር፥ ሆኖም በጌታ **ተፈተነ** የሚለውን ቃል፡ ልጠቀምበት እፈልጋለሁ። በእውነትም፡ "ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ እያንዳንዱ ልጅ በመጀመሪያ መፈተን፡ መሞከር፡ የልጅነት-ተግሣጽ መቀበል አለበት።" ከዚያም ፈተናው ከከበደ፡ እንዲሁም

በጣም ከባድ ነው ብለን ካሰብንና ካልሰማን፡ ተጠንቀቁ፡ ከዚያም ዲቃላ ልጅ እንሆናለን እንጂ፡ የእግዚአብሔር ልጅ አንሆንም አለ፡ ምክንያቱም እውነተኛውን፡ ዳግመኛ-የተወለደውን የእግዚአብሔር ልጅ ከወላጁ ሊለየው የሚችል ምንም ነገር የለምና፡ አያችሁ፡ የእሱ አካል ነው። ራሳችሁን ልትክዱ ትችሉ ይሆናል እንጂ፡ እሱን ከእንግዲህ ልትክዱት አትችሉም። አያችሁ፡ ልምዱ አላችሁ፡ ስለጥናችኋል ተፈትናችኋልም።

46 አሁን፡ ይህ ሰው ነቢይ በመሆኑ፡ ወደ እግዚአብሔር ጸጋ መድረስ ይችል ነበር፡ ነገር ግን ኢዮብ የሚያነበው መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረውም። እሱ... በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም ነበር፡ ነገር ግን በመገለጥና በራእይ ወደ እግዚአብሔር መድረስ ይችል ነበር። ያም የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ነበር።

47 አሁን፡ ከሕይወቱም ጥቂቱን ስንመለከት፡ እግዚአብሔር ሲባርከውና ታላቅ ሰው ሲያደርገው፡ እናገኛለን። ለምን፡ ሁሉም ሰው ያከብረው ነበር፡ ጥበቡም እንኳ፡ በጣም ታላቅ ሆኖ ነበር። ከእግዚአብሔር የሆነው መነሳሳቱ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን አጽንቶት ነበር፡ በጣም በግልጽ፡ ሰዎች እሱን ለመስማት ከየቦታው እስኪመጡ ድረስ። ከዚያም ሰይጣን ያንን ሰው መክሰስ ጀመረ። ለእያንዳንዱ መንፈስ ቅዱስ ላነሳሳው የእግዚአብሔር አገልጋይም የሚያደርገው እንደዚያው ነው፡ ሰይጣን ትክክል ባልሆነው በሚያደርገው ነገር ሁሉ እሱን ለመክሰስ ሁልጊዜ እዚያ አለ።

48 አሁን፡ ስለ ሕይወቱና፡ ፈተናዎቹ፡ እንዲሁም ስለ ታላቅ እምነቱ አይተናል። ኢየሱስ እንኳ፡ በምድር ላይ በመጣ ጊዜ፡ የኢዮብን ትዕግስት ጠቅሶ ነበር። እሱም አለ፡ "ስለ ኢዮብ ትዕግስት አላነበባችሁምን? " እምነት የተሰፋው ቃል እስኪፈጸም ድረስ በትዕግስት ይጠብቃል።

49 አሁን፡ እዚህ ጋር ኢዮብ፡ በፈተናዎቹ፡ በመከራዎቹ ሁሉ ውስጥ ካለፈ በኋላ እናስተውላለን... ውብ ቤተሰብ ነበረው፡ ከእሱ ተወሰዱበት። ጥሩ ጤንነት ነበረው፡ ከእሱ ተወሰደበት። በዚህ ሕይወት የነበረው ሀብት ሁሉ ተወሰደ። በአመድ ክምር ላይም ተቀምጦ፡ በሸክላ ስባሪ፡ እባጩን ይፈቀፍቅ ነበር። የገዛ ሚስቱ እንኳ፡ በእሱ ላይ ተናገረች፡ እሷም አለችው፡ "እግዚአብሔርን ሰድበህ፡ ለምን አትሞትም? "

50 እሱም፡ "አንቺ እንደ ሞኝ ሴት ትናገሪያለሽ" አላት። እንዲህም አለ፡ "እግዚአብሔር ሰጠ፡ እግዚአብሔርም ነሳ፡ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን!"

51 እዚህ ጋር፡ ሰይጣን ወደ እግዚአብሔር ፊት መጥቶ ነበር፡ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ፊት መምጣት ይችል ነበር፡ ክርስቲያኖችንም (ወይም፡ አማኞችን) ሁልጊዜ ይከስ ነበር። ስለዚህ ኢዮብን በብዙ ነገሮች ከሰሰው፡ እንዲህም አለ "ኢዮብ፡ እግዚአብሔርን ሊያገለግል የቻለበት ምክንያት፡ ሁሉም ነገር ለእሱ እየተሳካለት ስለሆነ ነው።" ነገር ግን እንዲህ አለ፡ "በእጄ ላይ፡ እንድጥለው ብቻ ከፈቀድክልኝ፡ ፊት ለፊት እንዲረግምህ አደርገዋለሁ።"

52 እግዚአብሔር በአንዱ አማኝ ላይ የነበረውን ያንን መተማመን፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። አያችሁ? እሱ... በሌላ አነጋገር፡ እግዚአብሔር ለኢዮብ፡ ማለቴ፡ ለሰይጣን እንዲህ አለው፥ "ልታደርገው አትችልም፡ ጻድቅ

ሰው ነው፡” የጻደቀ፡ “እሱ ጥሩ ሰው ነው፡ እሱ... በምድር ሁሉ ላይ እንደ እሱ ያለ ማንም የለም።” ኦህ፡ እግዚአብሔር ራሱ ለጠላቱ፡ “ባሪያዬ በጣም ፍጹም ነው፡ በምድር ላይ እንደ እሱ ያለ ሌላ ሰው የለም” የሚልለት እንዴት ያለ ሰው ነው። ኦህ፡ በምንም መንገድ ከቃሉ ወይም ከህልውናው ፈቀቅ እንደማንል አውቆ፡ እግዚአብሔር ሊተማመንብን የምንችል እንደዚያ ዓይነት ሰው፡ ብንሆን ኖሮ! ትክክል ሁኑ፡ እምነቱን በእኛ ላይ ሊጥል ይችላል።

53 አሁን፡ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ቃል በቃል፡ በትክክል የሚፈጽም ሰው ነበር። ሰይጣንም ያንን ያውቅ ነበር፡ ነገር ግን እንዲህ አለ፡ “በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠው፡ ፊት ለፊት እንዲረግምህ አደርገዋለሁ።”

54 ስለዚህ እግዚአብሔር ነገረው፡ እንዲህም አለ፡ “አሁን፡ በእጅህ ነው፡ ነገር ግን ሕይወቱን አትውሰድ።” ሰይጣንም በዚህ ላይ እስከሚችለው ድረስ ተንጠራራ። እያንዳንዱን ጓደኛውን፡ የነበረውንም ሁሉ፡ ከሞላ ጎደል ሕይወቱን ያዘ፡ ነገር ግን ሕይወቱን ሊወስድ አልቻለም። ነገር ግን ኢዮብ አሁንም በትክክል ጸንቶ ነበር፡ ወደ ኋላ መመለስ አልነበረም።

55 አያችሁ፡ አንድ ሰው፡ ወይም፡ አንድ ግለሰብ እግዚአብሔር መኖሩን ባመነበት በዚያ እውነተኛ በተገለጠ እምነት፡ ከእግዚአብሔር ጋር አንዴ በእውነት ከተገናኘ፡ በምንም ነገር፡ በምንም ጊዜ፡ በምንም ቦታ፡ ያንን ሰው ከእግዚአብሔር ሊለየው የሚችል ምንም ነገር የለም። ጳውሎስ ይመስለኛል፡ “ጠብም ቢሆን፡ ራብም ቢሆን፡ አደጋም ቢሆን፡ ሕያዋን ፍጥረታትም ቢሆኑ፡ ሞትም ቢሆን፡ ወይም ምንም ነገር በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል የለም።” ለዚያ ሕይወት ስለተመደባችሁ በእሱ ውስጥ በደኅንነት ተተክላችኋል።

56 ዳሩ ግን ሰይጣን ትንሽ ሊያጣምመው፡ ሊያስረውና፡ ይህን እንዲያደርግ ሊያስገድደው እንደሚችል አሰቦ ነበር። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር ማን እንደነበርና፡ እግዚአብሔር እንዴት ይወደው እንደነበር በነበረው ፍጹም መገለጥ፡ ጠበቀ! ሁኔታዎቹ ምንም ቢሆኑም፡ እምነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ጠበቀ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን አጥብቆ ይዞ ነበር፡ ያም መገለጥ ነው። ትናንት ማታ የተናገርኩት ያንን ነው።

57 አሁን፡ በሕንጻው ውስጥ ያላችሁ የታመማችሁ ሰዎች፡ ሽባ የሆናችሁ ሰዎች፡ ወይም እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁ ሰዎች፡ “የጻደቃችሁ” መሆናችሁን ያንን ዓይነት መገለጥ ማግኘት ስትችሉ፡ የጠየቃችሁትን ነገር በመጠየቃችሁ በእውነት ከጻደቃችሁ፡ እንዲሁም “በትጋት ለሚሹት ዋጋ የሚሰጥ ነው” ብላችሁ ስታምኑ፡ በእናንተ ውስጥ ሰር ከሰደደው ከዚያ እምነት ሊለያችሁ የሚችል ምንም ነገር የለም። አያችሁ? ነገር ግን፡ በመጀመሪያ፡ ለእናንተ መገለጥ አለበት።

58 በቅርቡ አንድ ሰው፡ አንድ የሰዎች ቡድን፡ ከእነሱም አንዳንዶቹ ዛሬ ማታ እያዳመጡ ነው፡ መጥተው ነገሩኝ፡ እንዲህም አሉ... እኔም፡ “ወደ ኬንታኪ ሂዱ፡ እዚያ ታች ነዳጅ አለ” እላቸው ነበር። እዚያ እንዳለ አውቅ ነበር፡ በራእይ አይቼው ነበር።

59 እንግዲህ፡ ወንድም ዴሞስና እነሱ ለረጅም ጊዜ አልሄዱም ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ በመጨረሻም፡ እንዲህ አሉ... ቴክሳስ ወደዚያ ከገባ በኋላ።

እነሱም እንዲህ ብለዋል፡ “አሁን ወደ ታች እየወረድን ነው።”

60 እኔም፡ “ከረጅም ጊዜ በፊት መሄድ ነበረባችሁ” አልኩ። ነገር ግን አላደረጉትም።

61 ዴሞስ እንዲህ አለ፡ “ያንን ባለማድረጌ፡ በዚያ ታላቅ ስህተት ሠርቻለሁ፡ ወንድም ብራንሃም” አለ።

62 እኔም፡ “ወደዚያ ወርዳችሁ ቢሆን ኖሮ፡ ሁሉንም ታገኙት ነበር” አልኩ።

63 እንግዲህ፡ ሊሰሙት አልፈለጉም ነበር። ከዚያም የመጀመሪያው... ከዚያም በዚያች ሌሊት ከመሄዳችን በፊት... ያ—ያ ምሳ እየበላንበት የነበረው ቦታ ነው። መንፈስ ቅዱስ በምድር ውስጥ ታላቅ ሰንጥቅ አሳየኝ፡ ያም በነዳጅ የተሞላ ነበር፡ በኬንታኪ ውስጥ የነበሩት እነዚህ ፍሰቶች ደግሞ እነሱ ነዳጅ እየሳቡባቸው ያሉት ትናንሽ የነዳጅ ክምችቶች ብቻ ነበሩ፡ ነገር ግን ይህኛው የመጣው ከዋናው ጅረት ነበር። እኔም፡ “ወንድም ዴሞስ፡ እዚያ ነው ያለው” አልኩ።

64 ስለዚህ ሊፈልጉት ሄዱ። እንዲህም አሉ፡ “ወደ ታች ውረድና የ—የነዳጅ ጉድጓዱ የት እንዳለ ንገረን።”

65 እኔም እንዲህ አልኩ፡ “ኦ፡ አይ! አይ! አይ!”

66 አያችሁ፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ ለንግድ አንጠቀምበትም። አይ! አይ! የት እንዳለ ሊነግረኝ ይችል ነበር፡ ነገር ግን ምንም አያስፈልገኝም። እሱን ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ እምነት እንኳ አይኖረኝም። አያችሁ? የሚያስፈልገኝ ቢሆን ኖሮ፡ ብጠይቀው፡ እንደሚነግረኝ አምናለሁ። ነገር ግን በመጀመሪያ፡ አያችሁ፡ ፍላጎቶቻችሁና ዓላማዎቻችሁ ትክክል መሆን አለባቸው። ለዚህ ምክንያቶች ሊኖሯችሁ ይገባል። እግዚአብሔር ስለጠየቃችሁ ብቻ እነዚያን ነገሮች አይሰጣችሁም። እንዲሁም በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመሆን፡ ለዚያ እውነተኛ ዓላማ ከሌለ በስተቀር በእምነት መጠየቅ አትችሉም። አያችሁ፡ መዳን ከፈለጋችሁ፡ ለምን መዳን ትፈልጋላችሁ? አያችሁ፡ መፈወስ ከፈለጋችሁ፡ መፈወስ የፈለጋችሁበት ምክንያት ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር ምን እየነገራችሁት ነው? ስትፈወሱ በሕይወታችሁ ምን ማድረግ ትፈልጋላችሁ? አያችሁ፡ ሊኖር ይገባል... ፍላጎትና ዓላማ ሊኖራችሁ ይገባል፡ እነሱም በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ትክክል መሆን አለባቸው። ከዚያም እምነት የሚገለጠው ያኔ ነው፡ እግዚአብሔርም በሉዓላዊ ጸጋው ያንን እምነት እዚያ ውስጥ ሲያኖረው፡ ያኔ ያበቃል። አያችሁ? አሁን አያችሁ?

67 አሁን፡ ያ ቃል እውነት እንዲሆን፡ ወንድሞች ወደዚያ ሲወርዱ፡ እነሱ... አንዱ ሰውዬ ሄዶ ብዙ ነገሮችን ገዛ፡ እንዲሁም የኪራይ ውሎችን ሸጠ፡ ሌላኛውንም በዚህ መንገድ አታለለው። እንዲህ አልኩ፡ “አያችሁ፡ አይሠራም።” አሁን **ትንቢቱ** እርግጠኛ እንዲሆን ብቻ፡ እነዚህ ሰዎች ጉድጓዳቸውን ከሚቆፍሩበት መቶ ያርድ ርቀት ውስጥ፡ አንድ ሰው እጅግ የሚፈልቅ ትልቅ የነዳጅ ጉድጓድ አገኘ። እሱም እዚያ ነው፡ በግማሽ ቀን ውስጥ አሥራ አንድ መቶ በርሜል ነዳጅ፡ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር፥ አሁንም እያወጣ ነው፡ ልክ በዚያው በዋናው ጅረት ላይ። ነገር ግን ትንቢቱ እውን እንዲሆን ብቻ፡ እዚያ እንዳለ የተነገረው ቃል፡ እዚያ ነበር። የቀሩት በሙሉ ማለት ይቻላል ደርቀዋል፡ በኬንታኪ ሁሉ

በየቦታው። ትናንሽ ኩሬዎች፡ ለጥቂት ጊዜ ይሰበቻቸዋል፡ ያልቃሉ። **ከዚህኛው** ተርፎ የፈሰሰው ብቻ ነው። እያችሁ?

68 ነገር ግን፡ ራስ ወዳድነት በመካከሉ ስለገባ፡ ዓላማዎቹ ስህተት ነበሩ፡ “**እንደዚህ** ይሆናል” በማለት ብዙ ነገሮችን ፈረሙ፡ ይህም ለእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚያደርጉት ቃል ገብተው ሳለ፡ ነገር ግን ለራሳቸው ያደረጉት ይመስላል። እያችሁ?

69 አይሠራም፡ ምንም የራስ ወዳድነት ነገር አይሠራም። ፍላጎቶቻችሁና ዓላማዎቻችሁ በትክክል፡ ፍጹም ትክክል መሆን አለባቸው፡ ከዚያም ለመጠየቅ፡ እምነት ይኖራችኋል። “ልባችን ባይኮንነን፡ በፊቱ ድፍረት አለን።” እያችሁ? እያችሁ፡ ድፍረት ሊኖረን ይገባል። “ይህን ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና እፈልገዋለሁ።” ከዚያም እምነት የሚንቀሳቀስበት መ—መተላለፊያ ያገኛል፥ እንደዚያ ካልሆነ ግን፡ አእምሯዊ፡ ምሁራዊ እምነት ነው ያላችሁት እንጂ፡ ከእግዚአብሔር የሆነ እውነተኛ እምነት አይደለም። ያ ምሁራዊ እምነት የትም አያደርሳችሁም። ስሜታዊ ሊያደርጋችሁ ይችላል፡ ነገር ግን የምትፈልጉትን ያንን ፈውስ አያስገኝላችሁም።

70 ስለዚህ፡ ኢዮብ፡ “ጻድቅ” መሆኑን እግዚአብሔር በሰጠው በእውነተኛው እምነት ራሱን ሲመረምር፡ እግዚአብሔር እንዲያደርግ የጠየቀውን ሁሉ አድርጎ ነበር። አሁን ለበሽታችን፡ እንዲጸለይልን ስንሄድ፡ እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገውን ሁሉ አድርገን ይሆን ብዬ አሰባለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስን እያንዳንዱን ነጥብ ተከትለናልን? ለአገልግሎት ልባችንንና ሕይወታችንን ለእርሱ ሰጥተናልን? ልትፈወሱ የፈለጋችሁበት ምክንያት ምንድን ነው? በቂ እምነት ማግኘት ያልቻላችሁበት ምክንያት ያ ነው፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም ምናልባት ይህን ነገር ከልባችሁ በቅንነት ለእግዚአብሔር ስላላደረጋችሁ ነው። ሕዝቅያስ እንዳደረገው፡ ለእግዚአብሔር ምክንያት ሰጡት፡ እሱ—እሱ መንግሥቱን በሥርዓት ለማስያዝ ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔርም ነቢዩን መልሶ ላከለትና ነገረው፡ እሱም ተፈወሰ። እያችሁ? ነገር ግን፡ በመጀመሪያ፡ እነዚያን ነገሮች ማስተካከል አለባችሁ።

71 ስለዚህ ወደ እነዚህ ቦታዎች እንደደረሳችሁና በእግዚአብሔር ቃል በመገለጥ፡ እግዚአብሔር እንድታደርጉት በሚጠይቀው ቃል፡ እንደተገለጠላችሁ ስታውቁ፡ ከዚያም እምነት፡ እውነተኛ እምነት ይኖራችኋል።

72 አሁን፡ ልክ አብርሃም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በነበረበት ጊዜ እንደነበረው ማለት ነው። ዘፍጥረት 17 ላይ፡ ይመስለኛል። እግዚአብሔር ለዚህ ያረጀ ሰው፡ አሁን፡ የዘጠና ዘጠኝ ዓመት አዛውንት ለሆነው፡ መቶ ዓመት ሊሞላው ለተቃረበው፡ እነዚያን ዓመታት ሁሉ ያንን የተሰፋ ቃል ሲጠብቅ ለነበረው ሰው ተገለጠለት። **ኤልሻዳይ**፡ “ባለ-ጡት” በሚለው ስም ተገለጠለት። ያም እንዴት ያለ ማበረታቻ ነበር፡ ሆኖም የተሰፋው ቃል በዚያን ጊዜ አልተፈጸመም ነበር። ነገር ግን፡ “አብርሃም፡ እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ፡ **ኤል ሻዳይ**፡ ‘ብርታትን-ሰጪ፡ ባለ ጡት አምላክ’ ነኝ።”

73 ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ፡ እንደሚጨነቀው፡ እንደታመመውና፡ እንደሚያለቅሰው፡ እንዲሁም በእናቱ ጡት ላይ እንደሚተኛው ትንሽ ሕፃን ነው። ብርታቱንም ከእሷ ጠብቶ ይመልሳል፡ ምክንያቱም እየጠባ ሳለ ይረካል፡

ምክንያቱም ያለውና የሚያውቀው ብቸኛው መድረሻ የእናቱ ጡት ስለሆነ ነው። ምንም ዓይነት የመድኃኒት መጠን አያውቅም። የመድኃኒት መጠን ልትሰጡት ትችሉ ይሆናል፡ እሱ ግን ይጮሃል ያለቅሳልም። ክንዱ ላይ መርፌ ብትወጉት፡ እሱ ማልቀሱን ይቀጥላል። ነገር ግን እሱን ሊያረካው የሚችለው ብቸኛው መድረሻ የእናቱ ጡት ነው።

74 እርሱም እንዲህ አለ፡ "አብርሃም፡ አንተ ያረጀህ ነህ፡ ብርታትህ አልቋል፡ ክንዶችህ ዝለዋል፡ ወንድነትህ ጠፍቷል፡ ነገር ግን እኔ እናትህ ነኝ። የተሰፋ ቃሌን ብቻ አጥብቀህ-ያዝ፡ እየጠበቅህም ሳለ እርካ። እረፍ!"

75 አሁን፡ እያንዳንዱ አማኝ መሆን ያለበት እንደዚያው ነው፡ ካንሰሩ ምንም ያህል ክፉኛ ቢይዛችሁም፡ በቂልቼር ላይ ምንም ያህል ጊዜ ብትቀመጡም፡ ከእነዚያ ነገሮች የትኛውም ቢሆን፡ ከእግዚአብሔር የሆነውን ያንን መገለጥ መረዳት ከቻላችሁ ብቻ! ከዚያም እንደሚፈጸም በማወቅ፡ የረካችሁ ሁኑ፡ ምክንያቱም እምነት የተሰፋውን ቃል በትዕግስት ይጠብቃልና። አያችሁ?

76 ኢዮብ ትክክል መሆኑን ያውቅ ነበር። እዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ እንደምናገኘው፡ እዚያ... እነዚህ ሰዎች ወደ እሱ መጡ፥ የቤተክርስቲያኑ አባላት። በአንድ ወቅት ለእሱ የተወደደ መስሎ የነበረው ሁሉ በእሱ ላይ ዞረ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ስለደረሱበትም፡ በሰውር ኃጢአተኛ ነው ብለው ሊከሱት ሞከሩ። ዛሬም ሰዎች፡ እንዲህ፡ ሲሉ ትሰማላችሁ፡ "ነግሬህ ነበር። ተመልከቱት! ምን እንደ... አያችሁ?" ያ ሙሉ በሙሉ እውነት አይደለም። አንዳንዴ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲፈትን ነው። በዚህ ሁኔታ፡ እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በምድር ላይ የነበረውን ከሁሉ የተሻለውን ሰው፡ ኢዮብን እየፈተነው ነበር። አሁን፡ እግዚአብሔር እዚያ አቆይቶት ነበር፡ ምክንያቱም ኢዮብ ከእግዚአብሔር ራእይ የተቀበለ ነቢይ መሆኑን፡ እግዚአብሔር እንዲያደርግ የነገረውን በትክክል እንዳደረገና እሱ... እግዚአብሔር ለእሱ የገባውን የተሰፋ ቃል የመጠበቅ ግዴታ እንደነበረበት ያውቅ ነበርና።

77 ኦህ! ክርስቲያኖች ሁሉ እንደዚያ መሆን አለባቸው። የሕይወታችን የመጨረሻ ትግል ሲመጣ፡ የሞት ጣር በጉሮሮአችን ሲሰማ፡ አሁንም ጸንተን በመቆም እግዚአብሔር፡ "በመጨረሻው ቀን ዳግመኛ አስነሳሃለሁ" ማለቱን ማስታወስ አለብን። አያችሁ? ያ—ያንን፡ ቦታችንን፡ ምንነታችንን፡ በክርስቶስ ውስጥ ያለንን ስፍራ፡ የትእዛዙን ቃል ሁሉ እንደጠበቅን እውቀን፡ ምስክርነታችንን መጠበቅ አለብን። "ወደ ውስጥ ለመግባት መብት ይኖራቸው ዘንድ ትእዛዛቱን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው።" አያችሁ? እንዲሁም ማንም ምንም ቢል፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለጻፈው ፈጣሪ በአክብሮት፡ በፍቅርና በፍርሃት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናየውን፡ እግዚአብሔር ያደረገልንን... እንድናደርግ የነገረንን፡ እያንዳንዱን ትእዛዝ፡ እንደጠበቅን ሰናውቅ ነው።

78 እኛ "ሰው የጻፈው ነው፡" እንላለን።

79 "የቀድሞ ሰዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው፡ ጻፉት።" አያችሁ? አያችሁ፡ እግዚአብሔር በሰው በኩል ጻፈው። ልክ አንድ ነቢይ ቃሉን ሲናገር፡ የነቢዩ ቃል አይደለም፡ በነቢዩ በኩል፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ አያችሁ። በእውነት እውነት ከሆነ፡ ሊፈጸም የሚገባውም በዚሁ ምክንያት ነው።

80 አሁን፡ ይህን ታላቅ ሰው እናያለን። እንዲሁም፡ አስታውሱ፡ ኢዮብ በዘመኑ የሚያነበው መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረውም። አልነበረውም! እሱ የተመራው በመንፈስ ብቻ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣለት ነቢይ ነበር። መንፈሳዊ መ—መመራት ብቻ ነበር የነበረበት፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑን ሥፍራውን ያውቅ ነበርና። አሁን፡ መሆን የነበረበት ብቸኛው ነገር፡ መንፈሳዊ ተነሳሽነት በእሱ ላይ እንዲወርድ ነበር። ከዚያም በመነሳሳት ስለነበር፡ የተናገረው ነገር እንደሚሆን ያውቅ ነበር።

81 ቤተክርስቲያንም፡ በሥርዓት ከሆነች (በሥርዓት ከተቀመጠች) እንደዚያው ናት፡ ይህም... መካኒክሱን አግኝታለች፡ የሚያስፈልጋት ዳይናሚክሱ ብቻ ነው። ዛሬ ማታ፡ መካኒክሱን ካዘጋጀን፡ ልባችንን ካስተካከልን፡ ልናደርጋቸው የምንችላቸውን ነገሮች አድርገን፡ እያንዳንዱን ቃል ከተከተልን፡ በጥምቀት እሱን ከተከተልን፡ እንድናደርግ በነገረን እያንዳንዱ ሥርዓት ውስጥ እሱን ከተከተልን፡ እያንዳንዱን መካኒክስ አዘጋጅተን፡ እዚያ ከቆምን፥ ከዚያም ዳይናሚክሱ እንዲበራ ዝግጁ ነን፡ ያንን ማድረግ የሚችለውም እግዚአብሔር ብቻ ነው፥ ያም "አሁን ተፈውሻለሁ፡" የሚለውን እምነት በልባችሁ ውስጥ መጨመር ነው። ከዚያም ሁኔታዎች ምን ቢሆኑም ምንም ለውጥ አያመጣም፡ ምንም ይሁን ምን ተፈውሳችኋል፥ ምክንያቱም እምነት ነው፡ በእምነት ተፈውሳችኋል።

82 በመንፈስ ተነሳሽነት ያገኘው፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነበረው። ራሱን ወደ ውጪ አውጥቶ፡ እግዚአብሔር ወደ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግበት መንገድ ነበረው። እንደጸደቀም ያውቅ ነበር። ስጦታ ነበር፡ ለሕዝቡ የተሰጠ ስጦታ ነበር፥ ለኢዮብ አልነበረም፡ ነገር ግን ለሕዝቡ ነበር። መለኮታዊ ስጦታዎች ሁሉ እንደዚያ ናቸው፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል ነው። ሁሉም ሰው ነቢይ እንዲሆን አልታዘዘም። ሁላችሁም አይደላችሁም... ለታመሙት እንድትጸልዩ አልታዘዛችሁም። ሁሉም ፓስተሮች እንዲሆኑ አልታዘዙም፡ ወዘተ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእነሱ የከፈተው መንገድ ነው። እሱም ዛሬ ጠዋት በትምህርቱ ውስጥ እንደነበረን ነው፡ እሱ... ምንም ያህል ቢነሳሳም፡ ምንም ያህል ቢመስልም፡ ምንም ያህል ጥሩ ቢሆንም... አንድ ሰው በሌላው ሰው መንገድ ውስጥ ጣልቃ የመግባት መብት የለውም፡ ዛሬ ጠዋት በስብሰባው ላይ ስንቶቻችሁ ነበራችሁ? እስቲ እጃችሁን ልየው። እያችሁ? እያችሁ፡ አትችሉም።

83 እነሆ ዳዊት፡ በሚችለው መጠን ሁሉ በመንፈስ ተነሳስቶ፡ ሕዝቡ ሁሉ እየጮሁና እግዚአብሔርን እያከበሩ ሳለ፡ ያም በትክክል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለሚመስል ምክንያት ነበር፡ ነገር ግን እሱ ትክክለኛው ሰው አልነበረም። ያ ምሪት መምጣት የነበረበት ለናታን ነበር እንጂ፡ ለዳዊት አልነበረም። እያችሁ፡ እሱ ናታንን እንኳ አላማከረም ነበር። ምን እንደተፈጠረ እያችሁ? እያችሁ፡ እኛ... እግዚአብሔር "ለባሪያዎቹ ለነቢያት ምስጢሩን ካልገለጠ በቀር ምንም አያደርግም" ብሏል።

84 ኢዮብም በዚህ ዘመን ይህ ነቢይ ነበር። አሁን፡ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ያደረገው ብቸኛው ነገር፥ ሁልጊዜ ጥበብን ቃሉን እና ምሪቱን ይሰጠው ከነበረው፡ አሁን ምንም ዓይነት ምሪት ሊያገኝ አልቻለም ነበር። ዳሩ ግን መካኒክሶቹን ሁሉ ያውቅ ነበር (የሚቃጠለውን-መሥዋዕት አቅርቦ ነበር፡

ለማድረግ ትክክል ነው ብሎ የሚያውቀውን ነገር ሁሉ አድርጎ ነበር)፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ሊያገኝ አልቻለም ነበር። ነገር ግን ዲያብሎስ ሊያናውጠው አልቻለም! ይኼውና አያችሁ።

85 አሁን፡ ሲጸልይላችሁ እንደዚያ ናችሁ። ተመልሳችሁ በሰልፍ ውስጥ ማለፍ፡ ወይም ሌላ ሰው እንዲጸልይላችሁ መሄድ አያስፈልጋችሁም። እግዚአብሔር እንድታደርጉ የነገራችሁን በትክክል እንዳደረጋችሁ ስታውቁ፡ አያችሁ፡ ከዚያም ያ የምሪት መንገድ እስኪከፈትላችሁ ድረስ ጠብቁ፡ እናም፡ "አሁን ተፈውሻለሁ!" እዚያ ውስጥ ሲወርድ፡ ያኔ ሁሉም ነገር ያበቃል። ኦህ፡ ምንም የጸሎት መስመር አያስፈልጋችሁም፡ ሌላ ምንም ነገር፡ በቃ አበቃ! ተገልጦላችኋል! አያችሁ?

86 ልክ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ እንደነበረው ያረጀ ነቢይ፡ "ጌታን ክርስቶስ ሳያይ ሞትን እንዳያይ፡" ለዚያ ሽማግሌው ጠቢብ፡ እንደተገለጠለት እናገኛለን። እርሱም ያንን አመነ፡ ጠበቀውም። ሰዎቹም እንዳበደ አሰቡ፡ ሽማግሌው አእምሮውን ስቷል አሉ። ነገር ግን እርሱ አሁንም አመነው! ምንም ነገር ከእርሱ ሊያናውጠው አልቻለም፡ እግዚአብሔር እንደገለጠለት ያውቅ ነበር፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር" ይላልና።

87 ስምዖንም በዚያች ደቂቃ ወደ ቤተ መቅደስ እየገባ፡ ተራምዶ ገባና ለእግዚአብሔር ምስጋና ሰጠ፡ እንዲህም አለ፡ "ባሪያህን በሰላም አሰናብተው።" ሕፃኑንም ባነሳ ጊዜ፡ "ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና።" አያችሁ፡ እንደሚያየው ያውቅ ነበር። በየቀኑ ምንም ያህል ሕፃናትን ቢጎበኝም፡ ከመሞቱ በፊት ክርስቶስን እንደሚያይ እግዚአብሔር እንደገለጠለት ያውቅ ነበር። ስምዖን ያንን አመነ።

88 አሁን **ለእናንተ** ለራሳችሁ፡ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል እንደተቀበላችሁ ሲገለጥላችሁ፥ መንፈሳዊ ተነሳሽነት፡ ክርስቲያኖች በመሆናችሁ፡ ሲወርድባችሁ፡ የጸሎት መስመር እንኳን አያስፈልጋችሁም። ነገሩ… የሚያስፈልጋችሁ ብቸኛው ነገር መካኒክሶቹ ሁሉ ሲዘጋጁ የተከፈተ ልብ መኖሩ ነው፡ ምሪቱም ወደ ውስጣችሁ እንዲገባ መፍቀድ ነው፡ ከዚያም አእምሯችሁን ምንም ሊለውጠው አይችልም፥ አግኝታችሁታል። ከዚያ ውጪ፡ ምንም አይጠቅምም።

89 አሁን አስተውሉ፡ ኢዮብ ምሪት የሚያገኝበት መተላለፊያ መንገድ ያስፈልገው ነበር፡ እርሱንም ክፍት አድርጎት ነበር። በምሪት፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነበረው። ራሱን ወደ ውጪ አውጥቶ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግበት መንገድ ነበረው። ከምሥራቅና ከምዕራብ እርሱን ሊያማክሩት እ—እንዴት ይመጡ እንደነበር አስተውሉ፡ ኢዮብ የተናገረው እውነት መሆኑን ሰላወቁ ሰዎች እርሱን ይፈልጉት ነበር። ያ ሰው እውነትን እንደተናገረ ያውቁ ነበር። ምክንያቱም፡ የተነበየው ነገር፡ የተፈጸመው ያው ነገር ነበር! ስለዚህም ሰዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጡ ነበር።

90 ወደ ገበያዎች እንደሚሄድ ይናገር ነበር፡ ከምሥራቅ የመጡት ወጣት መሳፍንትም ከእርሱ አንድ የማጽናኛ ቃል ለመስማት ብቻ፡ በፊቱ ይሰግዱ ነበር፡ ያም ታላቅና ኃያል ጥበቡን ነው፡ ምክንያቱም ሰውዬው ታማኝ መሆኑን ያውቁ ነበርና። ራሱን ከፍ አድርጎ መኩራራት አልፈለገም፡ የሚያስፈጽመው የራሱ

የሆነ ስውር ዓላማ አልነበረውም፡ በስውር የሚጎትተው ገመድም አልነበረውም፡ በእግዚአብሔር ፊት ታማኝ ነቢይ ብቻ ነበር። በእርሱም ላይ እምነት ነበራቸው፡ ሁሉም ሰው እንኳን ለትንሽ ጊዜ ብቻ እርሱን ለማነጋገር ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጡ ነበር። እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ስለዚህ ነገር ተናግሯል። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ይህ ሁሉ ስለ ምን እንደሆነ የሚነግረው ምሪት ጎድሎት ነበር። እግዚአብሔር እንዲሆን ፈቀደው እንጂ፡ አልነገረውም።

91 ከዚያም፡ አንድ ቀን፡ በዚያ ውስጥ ይህንን ተረድተናል፡ ይህም ጊዜው ያ እንደሆነ... ሁሉም ሰው፡ ልትረዷቸው እስከቻላችሁ ድረስ፡ “መልካም ነው” ይላሉ። ነገር ግን ከእናንተ ጋር አለመስማማት ሲፈልጉ፡ ችግር የሚመጣው ያኔ ነው። ነገር ግን እሱ ብቻውን ትክክል መሆኑን ያውቅ ነበር፥ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገረው የመሰማቱ፡ ያ የእምነቱ ምት፡ ያ እውነት መሆኑን ያውቅ ነበር። አዎን፡ ወዳጄ! የእግዚአብሔርን ድምፅ ያውቅ ነበር። በዚህ ጉዳይ ማንም ሊያታልለው አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም ያውቀው ነበርና። እሱ... ነገር ግን ሁልጊዜ እናንተ... አንድ ነገር ሲገለጥላችሁ፡ ምናልባትም ሰዎች ከሚያስቡት በተቃራኒ... አሁን፡ በነቢያት መስመር እየተናገርኩ ነው። እግዚአብሔር አንድን ነገር ሲገልጥ፡ ይህም፡ ከእግዚአብሔር ወጥቶ ለሕዝብ የሚታወቅ ምስጢር ካለ፡ በፍጹም በሴሚናሪ በኩል አይመጣም፡ በፍጹም በሰዎች ቡድን በኩል አይመጣም፡ መጥቶም አያውቅም። ሁልጊዜም የሚመጣው፡ የመጣውም፡ የሚመጣውም በአንድ ግለሰብ፡ በነቢይ በኩል ነው! አሞጽ 3፥7 ላይ፡ እያችሁ፡ “ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልገለጠ በቀር ምንም አያደርግም።”

92 አሁን፡ ኢዮብ የሆነ ችግር ገጥሞት ነበር፡ ነገር ግን፡ ምሪቱን በራሱ ላይ ሊያገኝ አልቻለም ነበር፡ ያም ያስጨንቀው ነበር፡ እንዲሁም ያ... እንደዚህ ዓይነት ፈተና ውስጥ ስትገቡ፡ ያኔ ነው ጠላት፡ ባሏችሁ ጓደኞች ሁሉ ውስጥ ማለት ይቻላል፡ የሚገባው። እነሱም ሊከሱት ጀመሩ። ኦህ፡ የከሰሱትን ጓደኞቹን ማወቁ ለእሱ በጣም አሳዛኝ ነገር ሆኖበት መሆን አለበት፡ ከዚያም ሰይጣን ሄዶ ራሱን ከጠላት ጋር ይቀላቀላል። ሰይጣን የሚመጣው ያኔ ነው፡ “በእጄ አድርገውና፡ በፊትህ እንዲረግምህ አደርገዋለሁ... መልእክቱን እንዲክድ አደርገዋለሁ። እንዲረግምህ አደርገዋለሁ። ወደ ኋላ ተመልሶ ‘ሁሉም ስህተት ነበር’ እንዲል አደርገዋለሁ።” ከዚያም በሚችለው ሁሉ፡ ባገኛቸው ታላላቅ ሰዎችና በጓደኞቹ ሁሉ ተጠቅሞ በሚችለው ሁሉ ፈተነው። ነገር ግን ኢዮብ ጸንቶ-ቆመ፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደሰማ ያውቅ ነበርና!

93 እግዚአብሔር ሆይ፡ ነገ ማታ ያንን፡ **የርግብ ክንፎች** የሚለውን እንድናገር፡ እርዳኝ። የሆነ ነገር የተናገረውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቻለሁ፡ ልክ በዚያው መንገድ ይፈጸማል! ልክ እንደነዚህ ሌሎች ነገሮች እንደተፈጸሙት ሁሉ፡ ይፈጸማል!

94 አሁን፡ ኢዮብ እንደሚፈጸም ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር “ጻድቅ” መሆኑን፡ እንደነገረውም ያውቅ ነበር። ነገር ግን እነሱ ኃጢአተኛ አደረጉት፡ ስለዚህ ምሪቱን ጠበቀ። ሰይጣን፡ በሁሉም—በሰዎቹ ውስጥ ገብቶ... አጽናኞቹ-ተብየዎቹ፡ ሊከሱት ጀመሩ፡ ዳሩ ግን ያ ትንሽ እንኳን አላናወጠውም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ለእሱ በጸናለት ጊዜ... በጆሮው መሰማት ስለ እግዚአብሔር ሰምቶ ነበር፡ ነገር ግን አንድ ቀን በሕይወቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ

ተቀምጦ ሳለ... እዚያም ተቀምጦ ሳለ፡ ሁሉም ሰው እየከሰሰው፡ የገዛ ሚስቱ እንኳን "ተሳስተሃል" እያለችው፡ እባጩን ይፈቀፍቅ ነበር። ኤሊሁም መጥቶ እግዚአብሔርን ስለሚከሰበት መንገድና ስለመሳሰሉት፡ ራስ ወዳድ በመሆኑ ገሰጸው።

95 ከዚያም በዚያን ጊዜ ነበር ምሪቱ በእሱ ላይ የወረደው፡ ያኔ ነው መብረቁ ብልጭ ማለት የጀመረው፡ ነጎድጓዱም ማንጎዳጎድ የጀመረው፡ ምሪቱ ነቢዩን የመታው ያኔ ነው፡ እሱም ተነሰቶ፡ እንዲህ አለ፡ "ቤዛዬ ሕያው እንደ ሆነ አውቃለሁ! በመጨረሻውም ዘመን በምድር ላይ ይቆማል። የቆዳ ትሎች ይህን ሰውነቴን ቢያጠፉትም እንኳ፡ ነገር ግን በሥጋዬ እግዚአብሔርን አያለሁ፡ እኔ ራሴም አየዋለሁ።"

96 እሱ አየ... ስለ ዛፎች፡ ስለ ዕፅዋት ሕይወት፡ እንዴት እንደሚሞትና እንደገና ሕያው እንደሚሆን ሲናገር ነበር፥ ውሃ እንደገና ይመልሰዋል፡ የውሃ ሽታ፡ የውሃ ጠረን፡ በዛፍ ወይም በመሰለ ነገር ላይ ውሃ የመፍሰሱ ውጤት፡ መሬት ውስጥ የገባ ዘርን እንደገና ያስነሳዋል። እንዲህ አለ፡ "ነገር ግን ሰው ይተኛል ነፍሱንም ይሰጣል፡ ልጆቹ ይከበራሉ እሱ ግን አያውቅም። ምነው መዓትህ እስኪያልፍ ድረስ" (ኢዮብ 14) "በመቃብር ውስጥ በሰወርኸኝ።" እንዲህም አለ፡ "ነገር ግን ሰው ከሞተ፡ ዳግመኛ ሕያው ይሆናልን? ለውጤ እስኪመጣ ድረስ በተመደበልኝ የሕይወቴ ዘመን ሁሉ፡ እጠብቃለሁ። አንተ ትጠራኛለህ፡ እመልሰልሃለሁም። የማላልፈውን ድንበር አድርገህልኛልና፡" ወዘተ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያውቅ ነበር። ዛፉ ሕያው ሲሆን ተመለከተ፡ ነገር ግን ሰው ሲሞት ምን ሆነ? እንደገና አልተነሳም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ይህን ቤዛ እያሳየው ነበር።

97 የሚማልድለት ሰው እንዳለ ለማየት ፈልጎ ነበር። ለብዙ ሰዎች ማልዶ ነበር፡ ነገር ግን አሁን ለእሱ ሊናገርለት የሚችል ሰው አለን? በኢዮብ ላይ፡ ወይም በኃጢአተኛ ሰውና በቅዱስ አምላክ ላይ እጁን ጭኖ፡ መንገድና ድልድይ ሊሠራ የሚችል ሰው ይኖር ይሆን? ወደ ቤቱ ሄዶ በሩን ማንኳኳት ይችላልን? እሱስ በሩን ከፍቶ ለጥቂት ጊዜ ያነጋግረው ይሆን?

98 ነገር ግን፡ ከዚያም፡ ምሪቱ በልቡ ውስጥ ሲወርድ፡ ያኔ እግዚአብሔርን ማየት ቻለ። መብረቁ-ብልጭ አለ፡ ነጎድጓዱ-ነጎደ። ይህ በሆነም ጊዜ፡ በእግሩ ቆሞ፡ እንዲህ አለ፡ "ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ አውቃለሁ! ቤዛዬ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናትም በምድር ላይ ይቆማል።" አያችሁ፡ እግዚአብሔር ለእምነቱ የሚሰጠውን ምላሽ ማየት ጀምሮ ነበር።

99 አሁን፡ እግዚአብሔርን ማየት እንችል እንደሆነ እናስባለን። እርሱን ማየት የምንችልበት መንገድ አለን? አሁን፡ እግዚአብሔር ኢዮብን የፈተነበት፡ ብቸኛው መንገድ ያ ነበር። እርሱም፡ "በጆሮ መሰማት ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ። ነገር ግን አሁን፡ በዓይኔ አየሁህ፡" አለ። የማይታይ የነበረው ራእይ አሁን የሚታይ ሆኖ ተገለጠ። ደመናው ሲንከባለል አየ፡ የመብረቁን ብልጭታ ሰማ፡ ወይም አየው። የነጎድጓዱንም መንጎድገድ አየ፡ ምናልባትም በጠራራ ቀን፡ እግዚአብሔርም በዚያ ደመናና በዚያ መብረቅ ውስጥ መሆኑን አየ። በተፈጥሮ ዓይኑ፡ እግዚአብሔርን ማየት ቻለ። አያችሁ፡ የማይታየው

የሚታይ ሆኖ ነበርና። ከዚያም የሌሎቹ የሚታየው ራእይ፡ ለተፈጥሮ ዓይን፡ ግልጽ ሆኖ ተረጋገጠ።

100 ልክ እምነት ከሥራ ጋር እንደሆነ፡ ትናንት ማታ እንደተነጋገርነው ነው። አብርሃም፡ የ... የሚያነበው መጽሐፍ ቅዱስም አልነበረውም፡ ነገር ግን ነቢይ ነበር፡ ራእዩና እምነቱ ነበረው። ልጅ ይወልዳሉ ብሎ ማሰቡ፡ በዚያ መንገድ ማሰቡ ለሌሎች ስህተት ይመስል ነበር። ነገር ግን ሕፃኑን ወለዱ፡ ምክንያቱም ይናገር የነበረው ስለ ሕፃኑ ስላየው ራእይ ነበርና፡ "አገኘዋለሁ! አገኘዋለሁ!" ነገር ግን ሕፃኑ በተወለደ ጊዜ፡ ሌሎች ሰዎች እሱ በራእይ ያየውን በዓይናቸው ማየት ቻሉ። በልባችሁ ባመናችሁት ነገር ላይ መሥራት ስትጀምሩ፡ ያኔ ሰዎች እግዚአብሔርን ያውቃሉ፡ በምታደርጉትም ድርጊት፡ ምን እየሆነባችሁ እንደሆነ ያውቃሉ። እግዚአብሔርን በዓይን የምታዩት በዚህ መንገድ ነው። ነገር ግን ለእሱ፡ ያደረገው መልካም ነገር ሁሉ፡ ለሌሎች ያደረገው ሁሉ ቢኖርም፡ የሚማልድለት ሰው አስፈልጎት ነበር። የሕፃኑ፡ ይስሐቅ መወለድ ሲመጣ፡ ወ—ወደዚህ የመራው ምሪት በራእይ ያየው ነገር በእርግጥም እውነት መሆኑን ሰዎች ማየት እስኪችሉ ድረስ ራእዩን አጽንቶት ነበር።

101 አሁን፡ አንዳንዴ እነዚህ ታላላቅ የእምነት ምቶች የሚመጡት ልክ በችግር ጊዜ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወደዚህ የሚገፋን ችግር ነው። ኢዮብንም ወደዚህ የገፋው ችግር ነበር። ለምን፡ በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ነበር። ልጆቹ ሞተው ነበር፥ ግመሎቹም። እንዲሁም ንብረቱ ሁሉ ጠፍቶና ወድሞ ነበር። ደግሞም የራሱ ሕይወት፡ ከራሱ አናት እስከ እግሩ ጥፍር ድረስ በእባጭ ተወሮ ነበር። እንዲህ እንዲሆን የገፋፋው፡ ችግር ነበር፡ ምሪቱም የመጣበት ያኔ ነበር።

102 ወንዶችና ሴቶች ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ዙሪያችሁን ብትመለከቱና ወደ ጌታ መምጣት ምን ያህል እንደተቃረብን ብታዩ። እናንተ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ወደ ጎን የተዋችሁ። ምናልባት ሰይጣን ሊያስመስለው በሚችለው በሆነ ስሜት፡ ወይም ባደረጋችሁት በሆነ ነገር ላይ ተደግፋችሁ ይሆናል፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃሎች ሁሉ ውስጥ ለመሄድ እውነተኛው መንፈስ በውስጣችሁ ሊኖራችሁ አይችልም። መንፈስ ቅዱስ አለኝ የሚል ሰው፡ እንዴት ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ቃል፡ "ትክክል አይደለም" ብሎ ሊክድ ይችላል? ልታደርጉት አትችሉም!

103 ምንም ያህል ሃይማኖተኛ ብትሆኑ፡ የቱንም ያህል ቤተክርስቲያናት አባል ብትሆኑ፡ ስማችሁ በስንት መጻሕፍት ላይ ቢሰፍርም፡ እውነተኛው መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ካለ (እርሱም ይህ የተገለጠው ቃል ነው)፡ ዘመኑን እና መልእክቱን ታያላችሁ፡ ምክንያቱም ይህን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው። ነገር ግን ያንን የሚያቀጣጥለው ብርሃን፡ ሊነካችሁ የሚገባ ምሪት መኖር አለበት። ደግሞም... መሬት ላይ፡ መሬት ላይ፡ መሬት ላይ ውሃ ብታፈሱ፡ ያን የሚያቀጣጥል ዘር በውስጡ ከሌለ፡ እንዴት አድርጎ አንዳች ሊያፈራ ይችላል? የሚበቅል ነገር የለውም። ማለት፡ የእግዚአብሔር ምርጦች ብቻ ያዩታል ማለት ነው።

104 የእግዚአብሔር ምርጦች በኖኅ ዘመን፡ በሙሴ ዘመን፡ በኢየሱስ ዘመን፡ በሐዋርያት ዘመን፡ በሉተር ዘመን፡ በዌስሊ ዘመን፡ በጴንጤቆስጤ ዘመን አይተውታል፡ ምክንያቱም ይህ ምሪት በወረደ ጊዜ በምድር ላይ የነበረው

ዘር ያ ነበርና። አሁን ሙሽራይቱን በአንድነት ለመሰብሰብ፡ መንፈሳዊ ምሪት እየፈሰሰ ባለበት በዚህ ጊዜ፡ የሚያዩት የተመረጡት ብቻ ናቸው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “አባት ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች፡ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ሰውረህ፡ መማር ለሚፈልጉት ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ።” አሁን፡ ምሪቱ በላዩ መውረድ አለበት።

105 አሁን፡ ምሪቱ በእሱ ላይ ሲወርድ፡ ያ ፈጸመው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አገኘው በቃ! አሁን፡ ግፊቱ በትክክል ሲበረታ፡ የእነዚህ ችግሮች ጊዜ እንደሚመጣ አይተናል። ደግሞም ዛሬ ዙሪያችሁን ስትመለከቱ፡ እየኖርንበት ያለውን ሁኔታ እዩት። በዘመናዊ ሰዶምና ገሞራ ውስጥ እየኖርን አይደለምን? ዓለም ወደዚያ አልተመለሰችምን? ያኔ በእሳት፡ የጠፋችው ያቺ የአሕዛብ ዓለም ነበረች። ኢየሱስ፡ በቅዱስ ሉቃስ፡ 17ኛው ምዕራፍ፡ 28ኛው፡ 29ኛውና፡ 30ኛው ቁጥር ላይ፡ ይህም፡ “በሰዶም ዘመን እንደ ነበረው፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት፡ በሰው ልጅ መምጣት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል” አላለምን? “በሚገለጥበት” ምንድን ነው? የሚታወቅ ምስጢር፡ መገለጥ ነው፥ ምስጢርን መግለጥ ወይም ማሳወቅ ነው።

106 አሁን፡ በቤተክርስቲያን ዘመናት ሁሉ ተሰውረው የነበሩት እነዚህ ነገሮች አሁን እየተገለጡ፡ እየታወቁ ነው። አሁን፡ እኛ ያንን ልንል እንችላለን፡ እግዚአብሔር ያንን ካላጸደቀው ግን፡ ያ ስህተት ነው። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ቃሉን የሚተረጉምለት ማንም ሰው አያስፈልገውም፡ እርሱ የራሱ አስተርጓሚ ነው። እርሱ፡ “ድንግል ትፀንሳለች” አለ፡ ፀነሰችም። እርሱ፡ “ብርሃን ይሁን” አለ፡ ሆነም። በሉተር ዘመን፡ በዌስሊ ዘመን፡ ወይም በጴንጤቆስጤ ዘመን ውስጥ እየኖርን አይደለም። የጴንጤቆስጤ ዘመን ስጦታዎች ወደ ቤተክርስቲያን የሚመለሱበት የተሃድሶ ጊዜ ብቻ ነበር፡ ነገር ግን እኛ በምሽት ጊዜ ውስጥ እየኖርን ነው፡ ሙሽራይቱ በምትጠራበት ጊዜ ውስጥ እየኖርን ነው።

107 ካቶሊኮች ሉተርን ማየት እንደከበዳቸው፡ እንዲሁም ሉተሮች ዌስሊን ለማየት፡ ደግሞም ጴንጤቆ-... ዌስሊዎች የጴንጤቆስጤ ዘመንን ለማየት እንደከበዳቸው ሁሉ፡ እንዲሁ ጴንጤቆስጤዎች **ይህን** ዘመን ማየት ይከብዳቸዋል። ሁልጊዜም እንደዚያ ነው የነበረው፡ ምክንያቱም የሚፈስው በተመረጠው ዘር ላይ ብቻ፡ ስለሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ያንን ነው። እነርሱ ሊያዩት አይችሉም፡ ኢየሱስ እንኳ ስለ እነርሱ ጸልዮ፡ “እነርሱ ዕውሮች ነበሩ፡ አላወቁትምም፡” አለ። ራእይ፡ በዚህ በሎዶቅያ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ከቤተክርስቲያን እንዲወጣ በተገፋ ጊዜ፡ እነርሱ “ዕራቁት! ድሆች! ጎስቋሎች! ዕውሮች! መሆናቸውንና አለማወቃቸውን” ይነግረናል። እንደገና፡ ሊያዩት አይችሉም፡ ሊረዱትም አይችሉም። በትውፊት በጣም ተተብትበዋል!

108 ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አፍ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አስታውሱ፡ ፍጥረትን በመናገር ወደ መኖር ያመጣው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡ ከዓለም መመሥረት በፊት፡ “ይሁን” ብሎ ቃላቱን የተናገረው እርሱ ነበር፡ ሆነም። እንዲህ ብሏልና፡ “እርሱ በዓለም ውስጥ ነበረ፡ ዓለምም በእርሱ ተፈጠረ፡ ዓለምም አላወቀውም። ነገር ግን ላወቁት ሁሉ፡ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።” ፈጣሪው ራሱ፡ ፈጣሪው ራሱ፡ አልዓዛርን ከሙታን ባስነሳው ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡

“ይህ እያስደንቃችሁ፡ በመቃብር ያሉቱ ሁሉ የሰው ልጅን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣልና፡ እነርሱም ይነሳሉ” አለ። “ብርሃን ይሁን” ያለው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር፡ “የሰው ልጅ ድምፅ በመቃብር ያሉትን ይቀሰቅሳቸዋል” አለ። በጊዜው መፈጸም አለበት። እርሱ፡ “ወንድና ሴት ይሁኑ” ብሎ ተናገረ፡ ወዘተ፡ ይህን ሁሉ፡ ከመፈጸሙ ከዓመታትና ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ነበር።

109 ምሪቱ ነቢዩን ኢሳይያስን መታው፡ እርሱም፡ “ሕፃን ተወልዶልናልና፡ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና። ስሙም ድንቅ መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ይባላል” አለ። ዓመታት አለፉ፡ ወራት፡ ዓመታት፡ ቀናት፡ ሳምንታት፡ ዓመታት አለፉ፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት አለፉ። ከሰምንት መቶ ዓመታት በኋላ፡ አማኑኤል በድንግል ተወለደ! ለምን? በእግዚአብሔር በተቀባ ነቢይ ከንፈሮች ስለተነገረ ነው፡ ዘር ወጥቶ ነበርና። እያችሁ? “በዚያችም ታላቅ ሰዓት፡” እንዲህ አለ፡ “ትፈልጋላችሁ... ራእይን ወይም ምልክትን ትጠይቁኛላችሁ።”

110 እርሱም፡ “እኔ ምልክትን እሰጣቸዋለሁ፡ የዘላለም ምልክትን፡ ‘ድንግል ትፀንሳለች፡’ የዘላለም ምልክትን” አለ።

111 አሁን፡ በእነዚያ በእውነተኛ የጭንቀት ሰዓታት ውስጥ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አብዛኛውን ጊዜ የሚንቀሳቀሰው ያኔ እንደሆነ አይተናል። እጁን ከማንቀሳቀሱ በፊት፡ የዕብራውያንን ልጆች በቀጥታ ወደ እሳቱ እቶን እንዲገቡ ፈቀደላቸው። ነገር ግን በተንቀሳቀሰ ጊዜ፡ ይንቀሳቀሳል።

112 አሁን፡ እዚህ በሉቃስ፡ በ—በ17ኛው ምዕራፍ፡ እንዲሁም በ30ኛው ቁጥር ላይ፡ እርሱ እንዲህ እንዳለ እናስተውላለን፡ “በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ ልክ ከሰዶምና ገሞራ በፊት እንዳደረገው የሰው ልጅ ራሱን እንደሚገልጥ፡ እንዲሁም ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ” ተናግሯል። ስለ ሙሴ ተናግሮ ነበር፡ ስለ... እንዲሁም ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ስለ ሙሴ ሳይሆን፡ ስለ ኖኅ ነበር። ሰዎቹ እንዴት “ይበሉና፡ ይጠጡ እንደነበርና፡ የመሳሰሉት እያደረጉ፡ ያገቡና ይጋቡ” እንደነበር። ከዚያም መጣና፡ እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ በሎጥ ዘመን እንደ ነበረው፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል” አለ። አሁን፡ ተመልከቱ፡ የሰው ልጅ ለአብርሃም ቡድን የተገለጠው፡ እንደ ሰው፡ በሰው ሥጋ መልክ እንዳለ ነቢይ፡ በልብሱ ላይ አቧራ እንዳለበት ተራ ሰው ሆኖ ነበር፥ አብርሃምም “ኤሎሂም” ብሎ ጠራው።

113 አሁን፡ ኢየሱስ እሳቱ ከመውደቁ ጥቂት ቀደም ብሎ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሰው ልጅ ለዚያው ዓይነት ቡድን፡ ለአብርሃም ንጉሣዊ ዘር፡ እንደገና እንደሚገለጥ እዚህ ቃል ገብቷል። አስታውሱ፡ ቤተክርስቲያን ከዚያ በኋላ ምንም ሌላ ምስክር አልተቀበለችም፡ አብርሃምና እነሱም አልተቀበሉም፡ ይጠብቁት የነበረው የተሰፋው ልጅ ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ መጥቶ ነበርና። እንዲሁም ቤተክርስቲያን የተሰፋውን ልጅ እየጠበቀች ነው፡ እርሱ ከዚህ አገልግሎት ቀናት በኋላ ወዲያውኑ ይመጣል፡ ከሰማያት ይገለጣል። አሁን፡ በጣም ግልጽ ሆኖ እናየዋለን፡ መሆንም አለበት። አሁን፡ ሊሆን የሚገባው ብቸኛው ነገር የሆነ የሚያነቃቃ ነገር፡ በሰው ውስጥ ገብቶ፡ እግዚአብሔር አጽንቶ ሊሆን ያለው ነገር ያ እንደሆነ የሚነግረውና የሚያሳየው ነገር ነው፥ እንዲሁም እናንተ ታደርጉታላችሁ...

114 ሙሴ እንዳደረገው፡ እነዚያ ልጆችን ነፃ ለማውጣት ፈቃደኛ አልነበረውም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ ተናገረው። ሊሄድ አልፈለገም ነበር፡ ነገር ግን መሄድ ነበረበት። ሙሴ እርሱ ታላቁ ይሖዋ እንደሆነ ሰምቶ ነበር። ነገር ግን ከዚያ እርሱን ማየት ቻለ፡ እርሱ በእሳት ዓምድ መልክ ነበር። "ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ።" በምን ውስጥ ነበር የታየው? ቃሉ በማጽናት።

115 እግዚአብሔር ለአብርሃም፡ "ሕዝቡ በማያውቁት አገር ለአራት መቶ ዓመታት በእንግድነት እንደሚቀመጡ፡ ነገር ግን በኃያል እጅ እንደሚያወጣቸው" ነግሮት ነበር።

116 እንዲሁም፡ አስተውሉ፡ ይህ የሚነድ ቁጥቋጦ ነቢዩ አብርሃም ይሆናል ብሎ የተናገረውን አጸና። ሙሴ እንዲህ አለ፡ "ስለ እሱ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁት!"

117 አሁን፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሰው ልጅ በሕዝቡ መካከል እንደሚመጣ ይህን **ሰምተናል** ሰዶም ከመጥፋቷ ጥቂት ቀደም ብሎ... ባደረገው በዚያው መንገድ ራሱን ለሕዝቡ እንደሚገልጥ ሰምተናል። የሰው ልጅ፡ ምን አደረገ? በሳራ ልብ ውስጥ የነበሩትን ምስጢሮች አውቆ ነበር። ለአብርሃምም የተስፋ ቃል ሰጠ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ ነበር፡ በብዙ የተለያዩ መንገዶችም አይቶት ሊሆን ይችላል (እንዴት እንዳነጋገረው አላውቅም፡ በሕልሞች ወይም በትንቢቶች)፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ አየው። "ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ።"

118 ቤተክርስቲያንም ስለ እግዚአብሔር ሰምታ ነበር፡ ስለ እርሱ፡ እንዲሁም ስላደረገው ነገር፡ ስለሰጣቸውም የተስፋ ቃላት እንብበዋል፡ አሁን ግን እኛ (ልክ ኢዮብ እንዳደረገው) በዓይኖቻችን እናየዋለን፡ "ስለ አንተ በመስማት ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ።" ማይ! እንዴት ያለ ልዩነት ነው።

119 ሙሴ፡ በዚያ ችግር ውስጥ ሆኖ፡ ጮኸ። በዘጸአት፡ 14ኛው ምዕራፍ፡ ከ13ኛው እስከ 16ኛው ቁጥር ድረስ ባለው፡ እናገኘዋለን፡ ሙሴ ከእስራኤል ልጆች ጋር በዚያ በታላቅ ጭንቀት ውስጥ ሆኖ፡ የምሪት ብልጭታ ነካው፡ የተናገረውንም ሳያውቅ፡ መናገር የነበረበትን ተናገረ። አያችሁ፡ "ዝም ብላችሁ ቁሙ የእግዚአብሔርንም ማዳን እዩ።" እግዚአብሔር ገና አላነጋገረውም ነበር። አያችሁ፡ ምሪት መጣበት።

120 እነሱም፡ "ለምን ወደዚህ አወጣኸን? በግብፅ መሞት ነበረብን። እዚያ ታች መቃብር ስላልነበረ ነውን? ወደዚህ አውጥተህ፡ እንድንሞት አደረግኸን፥ እስክንሞት ድረስ እንደ ባሪያዎች በሰላም መኖር እንችል ነበር፡ ነገር ግን ወደዚህ አወጣኸን" አሉ።

121 ነብዩ፡ ሙሴ፡ ወደ እግዚአብሔር መድረስ እንደሚችል አውቆ፡ በመንፈስ ምሪት፡ እንዲህ አለ፡ "ዝም ብላችሁ ቁሙ የእግዚአብሔርንም ማዳን ታያላችሁ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን፡ ዳግመኛ አታዩአቸውምና።" እንደሚሆን እንዴት አወቀ? እንዴት አወቀ? ምን እንደተናገረ አላወቀም ነበር።

122 ነገር ግን ልክ እንደተናገረው ወዲያውኑ፡ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያደርገው ነገረው። እንዲህም አለ፡ "ሙሴ፡ ወደ እኔ አትጩህ፡

በትርህን በእጅህ ያዝ በባሕሩም ላይ ዘርጋው፡ የእስራኤልንም ልጆች ‘እንዲራመዱ!’ ንገራቸው” አሜን!

123 ምሪት! ከታመማችሁ የሚነካችሁ በዚህ መንገድ ነው። ከተስቃያችሁ የሚነካችሁ በዚህ መንገድ ነው። የሆነ ነገር ይገለጥላችኋል፡ እንደተገለጠላችሁም ታያላችሁ፡ ድምፃችሁንም ከፍ አድርጋችሁ፡ “ተፈውሻለሁ” ትላላችሁ!

124 ከዚያም እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ይነግራችኋል፡ “ተነሱና መራመድ ጀምሩ።” አሜን! ከዚያም በዚያ መንገድ ማድረግ ስትችሉ፡ ሁሉም ነገር ያበቃል። እግዚአብሔር የሚያደርገው በዚያ መንገድ ነው፡ ከዚያም እግዚአብሔር በራሳችሁ በኩል ሲገለጥ ታያላችሁ።

125 ያንን እንዲያደርግ የነገረው እግዚአብሔር ነበር። አሁን፡ ከዚያም፡ እዚያ የነበሩት ሁሉ፡ እዚያ የነበሩት እስራኤል ሁሉ ሙሴን የነካውን ምሪት አዩ። እግዚአብሔር፡ ያንን ውኃ ከአንዱ ዳር ወደ ሌላኛው ዳር ሲያሸሸው፡ በገዛ ዓይናቸው አዩ። ያም የእሳት ዓምድ በቀጥታ ባ—ባሕሩን አቋርጦ መራቸው። እርሱ ስለ እግዚአብሔር ሰምቶ ነበር፡ ከዚያም እግዚአብሔርን አዩ።

126 ያ ሠራዊት ድል እየተደረገ፡ እና ፀሐይ እየጠለቀች ሳለ፡ ኢያሱ በችግር ሰዓት ውስጥ ነበር። ኢያሱ ነቢይ ነበር፡ እነዚያ ሠራዊቶች እንደገና አንድ ሆነው በእርሱ ላይ ቢመጡ፡ ብዙ ሰው እንደሚያጣ ያውቅ ነበር፡ ስለዚህ የሆነ ነገር መደረግ በነበረበት በዚያ የችግር ሰዓት... አንድ ነገር ብቻ ነበር፡ መሸሻቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ከቻለ፡ እያንዳንዳቸው፡ ድል፡ ያደርጋቸዋል። ዳሩ ግን ያንን ለማድረግ በቂ ብርሃን አልነበረም፡ ስለዚህ ኢያሱ ቆሞ፡ እጆቹን አንስቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ፀሐይ ሆይ፡ ጸጥ ብለሽ ቁሚ! ጨረቃም ሆይ፡ ይህን ጦርነት እስክጨርስ ድረስ በኤሎን ላይ ቁሚ” አለ። ፀሐይም ጸጥ ብላ ቆመች። ኢያሱ ሲናገር ሰሙት፡ ከዚያም እግዚአብሔርን፡ በተግባር፡ በገዛ ዓይናቸው አዩት። እውነት ነው!

127 አያችሁ፡ እርግጥ ነው፡ የማይቻል የሚመስለውን ነገር ማየት ለማመን የሚከብድ ነበር፡ ዳሩ ግን እውነት ነው። ነገር ግን፡ “ፀሐይ ጸጥ ብላ ቆመች፡” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። አሁን፡ እናንተ ሰዎች፡ ዓለም ትዞራለች ብላችሁ የምታስቡት ምን እንደምታስቡ አላውቅም፥ ነገር ግን፡ ለማንኛውም፡ “ፀሐይ ጸጥ ብላ ቆመች።” ምናልባት ኢያሱ እንዴት ሊያደርገው—ሊያደርገው እንዳለ፡ እግዚአብሔር እንዴት ሊያደርገው እንዳለ ለማሰብ ሞክሮ አያውቅም ይሆናል፥ የተናገረው ብቸኛ ነገር፡ “ፀሐይ ሆይ ጸጥ ብለሽ ቁሚ” የሚል ብቻ ነበር! ያንን የተናገረው፡ ምናልባትም የሚናገረውን ሳያውቅ ነበርን፡ ምክንያቱም ያንን የሰጠው እግዚአብሔር ነበር፡ እርሱም ሠራ።

128 በማርቆስ 11፥23 ላይም ተመሳሳይ ነገር ነው፡ “ለዚህ ተራራ ‘ተነቀል’ ብትሉት፡ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፡ ነገር ግን የተናገራችሁት እንደሚሆን ብታምኑ፡ የተናገራችሁትን ታገኛላችሁ።” ነገር ግን እዚያ ቆማችሁ በአእምሯችሁ እያመነታችሁ ልትናገሩት አትችሉም፡ ያንን ለመናገር መመራት አለባችሁ። አሜን!

129 አገላለጼን ይቅርታ አድርጉልኝ፥ ነገር ግን በዚያ ቀን፡ እዚያ ጫካ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ (እግዚአብሔርም ፈራጄ ነው፡ በዚህም መድረክ ላይ ሞቼ

ልወድቅ እችላለሁ)፡ ያ ጥቅስ በሕይወቴ ሁሉ ግራ አጋብቶኝ ስለነበር... በዚያ ጠዋት እዚያ ጫካ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ፡ ስለሱ እያሰብኩ ነበር፡ ያም ድምፅ ተናገረኝ፡ እርሱም፡ "ያ ቅዱስ ቃል እንደ ሌሎቹ ቅዱሳን ቃላት ሁሉ፡ እውነት ነው" አለኝ።

130 እንዲህም አሰብኩ፡ "እንግዲህ፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? "

131 እሱም፡ "አንተ ራስህ... " እ... እንዲህ አለ፡ "እንዲህ ይሁን በል፡ እንዲሁም ይሆናል። አትጠራጠር" አለኝ።

132 እኔም እዚያ ራቅ ብሎ ጫካ ውስጥ ተቀምጬ፡ ከሆነ ሰው ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። ሽኮኮዎች አልነበሩም፡ ለሦስት ቀናት እዚያ ቆይቻለሁ፡ በዚያ ሽኮኮዎች አልነበሩም። እኔም በሾላ ዛፎች ጥሻ ውስጥ ተቀምጬ ነበር። ሽኮኮዎች ወደዚያ አይመጡም... ሽኮኮዎችን የሚያድን ማንም ሰው፡ በሾላ ዛፎች ላይ እንደማይኖሩ ያውቃል። እኔም እዚያ ተቀምጬ ነበር፥ ነፋሱም በጣም በኃይል ይነፍስ ነበር፡ ከጠዋቱ በአሥር ሰዓት ገደማ፡ እኔም እንደገና እያሰብኩ ነበር።

133 እሱም፡ "እያደንክ ነው፡ አብርሃም አውራ በግ እንዳስፈለገው ሁሉ አንተም ሽኮኮዎች ፈልገሃል" አለኝ።

134 እኔም፡ "ሁልጊዜ እውነትን ነግሮኛል፡ ነገር ግን ይህኛው የሚያስቅ ይመስላል" ብዬ አሰብኩ። ከተቀመጥኩበትም ተነስቼ፡ ዙሪያዬን ሁሉ ተመለከትኩ፡ "የሚያነጋግረኝ ሰው የት አለ? " ምንም፥ ነፋስ በጣም በኃይል ይነፍሳል። በአሳቤም፡ "ምናልባት እንቅልፍ ወስዶኝ አልሜው ይሆን? አይ፡ አልተኛሁም። እዚያ ዛፍ ላይ ተደግፌ ተቀምጬ፡ እየተመለከትኩ ነበር፡ ወንድም ውድንና ወንድም ሶትማንን ማዶ ላይ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ከጠዋቱ በአሥር ሰዓት ገደማ እቀበላቸዋለሁ። ገበሬዎች በየቦታው ወጥተው፡ በቆሎአቸውን እየሰበሰቡ ነው።"

135 ዳግመኛም፡ ሲናገር ሰማሁት፡ "እያደንክ ነው፡ የሚታደንም ትፈልጋለህ። ስንት ያስፈልግሃል? "

136 እኔም በአሳቤ፡ "አሁን፡ ይህን ማብዛት አልፈልግም፡ ሦስት፡ ሦስት ሽኮኮዎችን ብቻ እጠይቃለሁ። ወጣት የሆኑ፡ ሦስት ቀይ ሽኮኮዎች። እፈልጋለሁ።"

137 እሱም፡ "እንግዲያውስ ይሁን በል" አለኝ።

138 እኔም፡ "ሦስት ወጣት ቀይ ሽኮኮዎችን አገኛለሁ" አልኩ።

139 እሱም፡ "በየትኛው-አቅጣጫ ይምጡ? "

140 "እንግዲህ፡" "እዚህ ድረስ ደርሻለሁ፡ የሚያነጋግረኝ የሆነ ነገር አለ"፡ ብዬ አሰብኩ። ልክ እኔ ሰናገር እንደምትሰሙኝ ማለት ነው። ይህን መጽሐፍ ቅዱስ በልቤ ላይ አድርጌአለሁ፡ ይህ እውነት እንደሆነ፡ የሰማይ አምላክ ያውቃል። እሱም... እኔም እንዲህ አልኩ፡ "እንግዲህ፡... " አንድ የሚያስቅ ቦታ መረጥኩ፡ (ጠመንጃዬን ካነጣጠርኩበት፡ አምሳ ያርድ ያህል ርቀት ላይ) ማዶ ላይ ተንጠልጥሎ የሚታይ ያረጀ የደረቀ ቅርንጫፍ ነበር።

141 እኔም፡ "የመጀመሪያው እዚያ ጋር ይሆናል" ስል፡ እዚያው አለ።

142 ዓይኖቼን አሸሁና ወደ ኋላ ተመለከትኩ (ጭንቅላቴን አዞርኩ)፡ እንዲህም ብዬ አሰብኩ፡ "ራእይ መተኮስ አልፈልግም።" ስለዚህ ዳግመኛ ዙሪያዬን ተመለከትኩ፡ ሽኮኮውም እዚያ ተቀምጦ ነበር። ጠመንጃዬ ውስጥ ጥይት አስገባሁ፡ ወደ ላይ አነጣጠርኩ፡ ጥቁር ዓይኑንም ማየት እችል ነበር፡ ወጣት ቀይ ሽኮኮ። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ "እ—እ... ምናልባት ተኝቼ ይሆናል፡ ከ—ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እነቃለሁ። አያችሁ፡ ስለዚህ ነገር እያለምኩ ነው።" እንግዲህ፡ ዝቅ ብዬ አነጣጥሬ፡ ሽኮኮውን ተኮስኩበት ከቅርንጫፉም ላይ ወደቀ። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ "እንግዲህ፡ አላውቅም።" እንዲህም አሰብኩ፡ "እንግዲህ፡ ወደዚያ ሄጄ ልፈልገው ይገባልን? " ወደ—ወደዚያም ተራምጄ ሄድኩ፡ እዚያም ወድቆ ነበር። አነሳሁት ደምም ፈሰሰው። ታውቃላችሁ፡ ራእይ አይደማም። ስለዚህ አነሳሁት፡ ሽኮኮም ነበር። ሰውነቴ በሙሉ፡ በጣም ደነዘዘ።

143 ዙሪያዬንም ተመለከትኩና፡ እንዲህ አልኩ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ያ አንተ ነበርክ!" እንዲህም አልኩ፡ "ስለዚህ ነገር፡ አመሰግንሃለሁ። አሁን እወጣና... "

144 እሱም፡ "አንተ **ያልከው** ግን! በተናገርከው ትጠራጠራለህን? 'ሦስት' ብለህ ተናግረህ ነበር። አሁን ቀጣዩ ከየት ይውጣ? "

145 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ "እንግዲህ፡ እያለምኩ ከሆነ፡ እቀጥላለሁ።"

146 ስለዚህ እንዲህ አ—አልኩ... ማዶ ላይ፡ በዚህ መርዛማ አረግ የተጠቀለለ ያረጀ የዛፍ ጉቶ መረጥኩ። በዚያ ውስጥ በፍጹም ሽኮኮ አታገኙም። ስለዚህ፡ "ቀጣዩ ከዚያ መርዛማ አረግ ውስጥ ይውጣ፡" ያም ወጣት ቀይ ሽኮኮ ትኩር ብሎ እያየኝ እዚያ ተቀምጧል። ጠመንጃዬን አስቀመጥኩና፡ ዓይኖቼን አሸሁ። እንደገና ዞር አልኩና፡ እንዲህ ብዬ አሰብኩ... ተቀምጦ፡ ጭንቅላቱን ወደ ጎን አዞረ። ሽኮኮውን ተኮስኩበት፡ ከዚያም ወደ ቤቴ መሄድ ጀመርኩ።

147 ነገር ግን እንዲህ አለ፥ "አንተ ያልከው 'ሦስት'! በተናገርከው ትጠራጠራለህን? "

148 እንዲህም አልኩ፡ "አይ፡ ጌታ ሆይ፡ በተናገርኩት አልጠራጠርም፡ ምክንያቱም አንተ እያረጋገጥከው ነውና።"

ይህ ግራ ያጋባኝ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፥ "**እኔ** ካልኩ ሳይሆን፡ **አንተ** ካልህ።" **ኢየሱስ** ከተናገረው ሳይሆን፡ **አንተ** ራስህ ከተናገርከው።

149 አሰብኩም፡ "በሆነ መንገድ ወደዚያኛው መስመር ገብቻለሁ፡ ብቻዬን ስለሆንኩ እርሱ እዚህ እንዳለ አውቄአለሁ።" እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ "እስኪ ይህኛውን ደግሞ፡ የማይመስል ላድርገው።"

እንዲህ አልኩ፡ "አንድ ቀይ ሽኮኮ **ከዚያ** ኮረብታ ላይ ይውረድ፡ **በዚህ** መንገድ ወደ ታች ይምጣ፡ በአጠገቤ አልፎ፡ ወጥቶ፡ **እዚያ** ቅርንጫፍ ላይ ይቀመጥ፡ **እዚያ** ታች ያለውን ያንን ገበሬንም ይመልከት።" እነሆም ከኮረብታው ወረደ፡ በቀጥታ ወጥቶ፡ ተቀመጠ፡ ገበሬውንም ተመለከተ። እኔም ተኮስኩበት።

150 ሰይጣንም እንዲህ አለኝ፡ “ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ይኸውልህ፡ ጫካውኮ በእነሱ ተሞልቷል።” ከዚያም እስከ አሰራ ሁለት ሰዓት ድረስ ተቀመጥኩ፡ ዳሩ ግን ሌላ ምንም ነገር አልተፈጠረም። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር... እሱ ራሱ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ መሆኑን ነው!

151 አሁን በጀፈርሰንቪል ውስጥ፡ እያዳመጡ ያሉ፡ ራይት የሚባሉ ቤተሰብ አሉ። እኔና ወንድም ውድ እነሱን ለማየት ወረድን። ለቤተክርስቲያኒቱ የቁርባን ወይን ያዘጋጃሉ። ምስኪኗ ኤዲት በዚያ ክፍል ውስጥ ተቀምጣ የኖረች፥ በሕይወቷ ሙሉ ታማ የኖረች፡ ሽባ ልጅ ነበረች፡ ስለዚህ እንዲፈውሳት ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንማጸን ነበር። እህቷ፡ ባሏ የተገደለባት፡ መበለት፥ ስሟ ሃቲ ይባላል፡ በጣም ትሁት የሆነች ምስኪን ሴት። ወንድም ባንክሰና እኔ ጥንቸል ልናመጣላት ወደ ውጪ በወጣንበት ጊዜ፡ ትልቅ የቼሪ ኬክ ጋግረው ነበር፥ አስቀምጠውም አበሉኝ።

152 ሁላችንም በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠን፡ ስለዚህ ጉዳይ እየተነጋገርን ነበር፡ ይህም ከጥቂት ቀናት በፊት ነው። በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠን፡ ስለዚህ ጉዳይ እየተነጋገርን ሳለ፡ ድንገት፡ “ምን ሊፈጠር ይችል ነበር” አልኩ? እንዲህ አልኩ፡ “ወንድም ራይት፡ አንተ ያረጀህ ሰው ነህ፡ በሕይወትህ ሙሉ ሽኮኮዎችን ስታድን ኖረሃል። ወንድም ሼልቢ፡ አንተ የተዋጣልህ የሽኮኮ አዳኝ ነህ። ወንድም ውድ፡ አንተም እንዲሁ ነህ። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ አድኜያቸዋለሁ። በሾላና በግራር ጥሻ ውስጥ ሽኮኮ አይታችሁ ታውቃላችሁን? ”

153 “አይ፡ ወዳጄ።”

154 እኔም፡ “እዚያ አልነበሩም” አልኳቸው። እንዲህ አልኩ፡ “እኔ የማውቀው ብቸኛ ነገር፡ ያው አምላክ መሆኑ ነው። አብርሃም አውራ በግ ባስፈለገው ጊዜ፡ እርሱ **ይሖዋ-ይሬ** ነበር፡ ‘ለራሱ ሊያዘጋጅ’ ችሏል።” “ይህም ተመሳሳይ ነገር እንደሆነ አምናለሁ፡” አልኳቸው።

155 እዚያ ተቀምጣ የነበረችው ምስኪን ሃቲ፡ እንዲህ አለች፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ ሌላ ነገር ያልተቀላቀለበት እውነት ነው!”

156 ትክክለኛውን ነገር ተናገረች! እሷ ይህን ስትናገር፡ መንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመተላለፊያው ውስጥ ወረደ፡ እያንዳንዳቸውም ተሰማቸው። ተነሳሁና፡ እንዲህ አልኩ፡ “እህት ሃቲ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ሲሮፊኒቃይቷ ሴት እንደተናገረችው ትክክለኛውን ቃል ተናግረሻል። መንፈስ ቅዱስ አሁን እያነጋገረኝ ነው፡ የልብሽን መሻት እንድሰጥሽም ነግሮኛል።” እንዲህ አልኳት፡ “አሁን፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንኩ፡ ከሆንኩ፡ ይፈጸማል። የእግዚአብሔር አገልጋይ ካልሆንኩ ግን፡ ውሸታም ነኝ፡ አይፈጸምምም፡ አታላይ ነኝ።” እንዲህም አልኳት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ መሆን አለመሆኑን፡ አሁን ፈትነሽ እወቂ።”

157 እሷም፡ “ወንድም ብራንሃም” አለች፡ (ሁሉም ያለቅሱ ነበር)፡ እሷም አለች፡ “ምን ልጠይቅ? ”

158 እኔም፡ “እዚያ የተቀመጠች ሽባ እህትሽ አለች” አልኳት።

159 እሷ በስጦታ መልክ ያኖረችውን፡ ለእሷ ለመስጠት፡ ኪሴ ውስጥ ሃያ ዶላር ነበረኝ። ሴትዮዋ በዓመት ሁለት መቶ ዶላር የሚያህል ካፒታል እንኳን አታገኝም፡

በዚያች ትንሽ፡ ያረጀች፡ ደሃ እርሻ ላይ፡ እሷና ሁለት ልጆቿ ይኖራሉ። ልጆቿ መደበኛ ‘ፍንዳታዎች’ ሆነው ነበር፡ የትምህርት ቤት ዘመን፡ ታውቁታላችሁ፡ እናታቸውን የሚሳደቡ፥ የአሥራ አምስት፡ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጆች ነበሩ። ደግሞም፡ ኦህ፡ እዚያ ቆመው በምለው ነገር ላይ ይስቁ ነበር።

160 እኔም እንዲህ አልኩ፡ “አባትና እናትሽ አርጅተው እዚህ ተቀምጠውልሻል። ምንም ገንዘብ የለሽም። ገንዘቡን ጠይቂ፡ ጭንሽ ላይ ከወረደና ካልወረደ እይ። ስለ እህትሽ ጠይቂ፡ ተነስታ መራመድ አለመራመዷንም እይ።” ልክ እንደ ኢዮብ፡ ያኔ አንድ ነገር ተረዳሁ፡ እሱ ሲነካችሁ የምታውቁት የሆነ ነገር አለ። እንዲህ አልኩ፡ “አውቃለሁ! እዚህ አሥር በሚጠጉ ሰዎች ፊት ቆሜያለሁ፡” አክዬም፡ “ይህ ካልተፈጸመ፡ እንግዲያውስ ሐሰተኛ ነቢይ ነኝ።”

161 እንዲህም አለች፡ “ምን ልጠይቅ? ”

162 እንዲህ አልኳት፡ “ውሳኔሽን ማድረግ የአንቺው ድርሻ ነው። እኔ ልወስንልሽ አልችልም።”

163 ምስኪኗ ሴት፡ ዙሪያዋን ቃኘች። ድንገትም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ በልቤ ውስጥ ያለው ከሁሉ ታላቁ ምኞት የሁለቱ ልጆቼ መዳን ነው፡” አለች።

164 እንዲህ አልኳት፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልጆችሽን ሰጥቼሻለሁ።” እነዚያ የሚያሾፉ፡ የሚስቁና፡ የሚያላግጡ ልጆችም እናታቸው ጭን ላይ ወደቁ፡ ሕይወታቸውንም ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሰጡ፡ እዚያውም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

165 ለምን? ያ እውነት ነውና! በሀገሪቱ ሁሉ ባሉ በእነዚህ ሰዎች ፊት፡ እግዚአብሔር ሊገድለኝ ሥልጣን አለው። እዚህ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ እንዲሁም በጀፈርሰንቪል ያላችሁ፡ አሁን በታበርናክሉ ውስጥ፡ “አሜን” ተብሎ ሲያስተጋባ መስማት እችላለሁ! ምክንያቱም ልክ እዚያው ተቀምጠው እያዳመጡት ነውና። አያችሁ፡ ምክንያቱም እውነት ነውና! ምንድን ነው? እግዚአብሔር፡ በሉዓላዊ ጸጋው ሲያደርገው ነው፥ ይፈጸማል! ከዚያ ውጪ፡ አይፈጸምም።

166 በዚያ ወሳኝ ሰዓት... ሳውቃቸው የነበሩትን ሰዎችና ሕዝቦች አሰቡ። እግዚአብሔር ታዋቂዎችን ሁሉ፡ እንዲሁም ሁሉንም ነገር አልፎ፡ ስሟን እንኳ በቅጡ መፈረም ለማትችል፡ አንዲት ድሃ፡ ትንሽ ያረጀች ትሁት ሴት ለመስጠት፥ እሷም ምን እንደምትጠይቅ ያውቅ ነበር። ያም ከሁሉ የላቀው ነገር ነበር፥ ምክንያቱም እህቷ አሁን ሞታለች፡ እናቷና አባቷም መሞታቸው አይቀርም፡ ገንዘቡም ይጠፋ ነበር፡ የልጆቿ ነፍሳት ግን ዘላለማዊ ናቸውና! ያም እነሱ ያንን የሚይዙበት ሰዓት ነበር። ልክ፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልጆችሽን ሰጥቼሻለሁ” እንዳልኩም፡ እዚያው እናታቸው ጭን ላይ ወደቁ። እዚህ ውስጥ ይህ እውነት መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ፡ ታውቁታላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? በትክክል። አዎ። ለምን? ምሪት!

167 አሁን፥ “ሽኮኮዎችን መፍጠር እንደምትችል፡ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፥ አውራ በግ መፍጠር እንደምትችል፡ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፥ አሁን ግን በገዛ ዓይኔ፡ እየሁህ!” መገለጡ፡ ራእዩ የሚታይ ሆነ። እግዚአብሔር ምንም ነገር ቃል ሲገባ፡ የሚያደርገው ያንኑ ነው።

168 አስተውሉ፡ ምናልባትም እንደ ኢያሱ፡ እናንተም የምትፈልጉት ነገር ይኖራችኋል። ፍላጎት ነበረው፥ ስለ ሁኔታዎቹ በፍጹም አላሰበም፡ ተናገረው፡ እግዚአብሔርም ነበር! ፀሐይ ጸጥ ብላ እንደቆመች ታምናላችሁን? እኔም አምናለሁ። ያንን እንዴት አደረገው? ለማወቅ አትሞክሩ፡ ዳሩ ግን አድርጎታል። ኢያሱ ያንን አደረገ፡ እጆቹንም አነሳ፥ በዚያ ወሳኝ ሰዓት ወደ እግዚአብሔር መድረሻ ነበረው፡ የተፈጠረውም ያ ነበር። ወቅታዊ ነበር። የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ የነገሩን አስፈላጊነት አይቶት ነበር፡ ኢያሱም ያንን እንዲናገር ገፋፋው። ያው እግዚአብሔር የአብርሃምን አስፈላጊነት አየ። ያው እግዚአብሔር ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለእኔ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን አየ፡ **ያ** ቃልም እንዲሁ፡ እውነት ነው! ያው እግዚአብሔር የእነዚያን ሁለት አስቀድመው የተወሰኑ ልጆች አስፈላጊነት አየ፡ ያንን ያረጋገጠበትና ቃሉን ያጸናበትም ያች ቅጽበት ነበረች።

169 በቅዱስ ማርቆስ 14 ላይ፡ አንዲት ሴት በእርሱ እንዳመነች እናያለን፡ ፍላጎት ነበራት እርሱ እግሮቹ መታጠብ እንዳስፈለገው አየች፡ ወደ ተግባር ለመግባት መነሳሳት ብቻ አስፈልጓት ነበር። አሁን ከመጨረሳችን በፊት... በጥሞና አዳምጡ። ወደ ተግባር ለመግባት መነሳሳት ብቻ አስፈልጓት ነበር፡ ምክንያቱም ስለ እርሱ አስቀድማ ሰምታ ነበርና። "የአንዲትን ሴት ኃጢአት፡ ጋለሞታን ይቅር እንዳለ" ሰምታ ነበር። እንዲሁም፡ 'ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት ማን ነው? አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት' ማለቱን።" ስለ እርሱ ሰምታ ነበር፡ አሁን ግን አየችው። እርሱን ለማገልገል ተነሳሳች። ልትሆኑት የሚገባችሁ ብቸኛው ነገር ያ ነው።

170 መንፈስ ቅዱስ "ኃጢአተኛ ነህ" ብሎ ይነገራችሁ! መንፈስ ቅዱስ "ተሳስተሃል" ብሎ ይንገራችሁ! መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጻሕፍት "በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ተሳስተሃል" ብሎ ያረጋግጥላችሁ! እንዲሁም... ምክንያቱም እሱ በእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባለ በአንድ ቀጥተኛ መተላለፊያ በኩል ብቻ ነው የሚያንቀሳቅሰው፡ ለምንም ብሎ ጥሶ አያልፍም። እንደዚያ ካደረጋችሁ፡ በፍጹም ምንም አይጠቅማችሁም። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ያንን ሊያበራላችሁ ይችላል፡ በዚህ ሳምንት እንዳየነው ግን፡ ነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ካልሆነች፡ ለምንም አትጠቅምም። አስታውሱ፡ በመጨረሻዎቹ-ቀናት የተቀቡ ሐሰተኛ ይነሳሉ፥ ሐሰተኛ ኢየሱሶች አይደሉም፡ ሐሰተኛ ክርስቶሶች (የተቀቡ) ናቸው፡ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።

171 አስተውሉ፡ ለእርሱ የምታደርገው አገልግሎት ነበራት። ስለ እርሱ ሰምታ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኖቿ አየችው። የምታደርገው አገልግሎት ነበራት፡ ያንን የምታደርግበት ምንም ነገር አልነበራትም። ስለዚህ እንዴትም አገልግሎቱን ለማድረግ፡ ወደ ፊት ሮጠች፡ እግዚአብሔር እግሮቹን የምታጥብበትን ውኃና ፎጣ አቀረበላት። ሕይወቷ ሙሉ፡ ስለ ሕያው እግዚአብሔር ሰምታ ነበር፡ ነገር ግን አሁን በዓይኖቿ አየችው። እርሱ መሆኑን አወቀች፡ መንፈሳዊ ምሪትም ነካትና፡ እንዲህ አለች፡ "**ይህ** መልእክተኛው ነው!" አገልግሎት አስፈልጎት ነበር (የምታገለግልበት ምንም ነገር አልነበራትም)፡ እግሮቹ ቆሽሸው ነበር። ዳሩ ግን ለማንኛውም አገልግሎት ልታደርግለት፡ ወደ ፊት ሮጠች፡ ምክንያቱም ያንን ለማድረግ ተመርታ ነበርና።

172 ኩብላይ የቤተክርስቲያን አባል ሆይ፡ የሐይማኖት ተቋም ሰው ወይም

ሴት ሆይ፡ ኢየሱስ ዛሬ ማታ የሚፈልገውን ማየት አትችሉምን? የመንፈስ ምሪት ከዳሰሳችሁ፡ ይህን የምታደርጉበት ሰዓት አሁን ነው። እሷ ግን በዓይኖቿ አየችው። በዚያ የነበሩት ሌሎች በእርሱ ላይ ያሾፉበት ነበር። በመልእክቱ አላመኑም ነበር። በግልጽ ለመናገር፡ አዘጋጁ፡ አዘጋጅ-ፓስተሩ፡ ሽማግሌው ስምዖን፡ በእርሱ ላይ ለመቀለድ ጋብዞታል። ነቢይ መሆኑን አላመኑም ነበር።

173 ስለዚህም ዲያብሎስ ይህንን እንዲናገር ልክ ትክክለኛውን ሁኔታ ያመቻቸለት በነበረ ጊዜ፡ በልቡ እንዲህ አለ፡ "ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ፡ በእግሩ አጠገብ ያለችው ሴት ምን ዓይነት ሴት እንደሆነች ባወቀ ነበር። ነቢይ ቢሆን ኖሮ!" አያችሁ፡ እርሱ ማን እንደነበር ለእርሱ እንኳ አልተገለጠለትም ነበር። ምንም ዓይነት ምሪት ሊመታው አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም እዚያ የሚነካው ምንም ነገር አልነበረምና። ነገር ግን እሷን ነካት!

174 ዓይኖቿ ከእርሱ ትችት በላይ አይተው ነበር። እርሱ መሆኑን አመነች፡ አያችሁ፡ የነቢያት ቃል። ያ የነቢያት ቃላት ሁሉ፡ በእርሱ እንደ ጸና አውቃ ነበር። በምድር ላይ እንዳለ ሰምታ ነበር፡ ነገር ግን አሁን አየችው። ምን እንዳደረገች ተመልከቱ። ቃሉ ሥጋ ሆኖ አየች፡ መሢሑን፡ አማኑኤልን። ለእምነቷ ምት መተንፈሻ በሰጠች ጊዜ (በምትኖርበት ዘመን፡ እርሱ ማን እንደሆነ ለተገለጠው መገለጥ፡ ይህም እንደ እሷ ላሉ ኃጢአተኞች እርሱ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን)፡ እንዴት እንደምታደርገው ሳታውቅ ፍላጎቶቹን ለማገልገል ወደ ፊት ወጣች።

175 እውነተኛ ፈውስ የሚመጣው በዚያ መንገድ ነው፡ ሲገለጥላችሁ ማለት "እርሱ ስለ አንተ መተላለፍ ቆሰለ፡ ስለ አንተ በደል ደቀቀ፡ በእርሱም ቁስል **አንተ** ተፈወስክ" ተብሎ ሲገለጥልህ። የእርሱን ሕልውና እዚህ እንድታዩት ሲገለጥላችሁ፡ የቅዱስ ማርቆስ 11፡ ወይም፡ የቅዱስ ሉቃስ 17፥30፡ ልክ ከሰዶም በፊት እንዳደረገው በመጨረሻዎቹ ቀናት (በሕዝቡ መካከል፡ በሰው ሥጋ) ራሱን እንደሚገልጥ። ያንን ስታዩ፡ የሆነ ነገር ይነካችኋል!

176 ሐኪሙ፡ "ካንሰሩ አሁንም አለ" ሊል ይችላል።

177 በሽተኛውም፡ "እ—እ—እ—እ—እ—እንዴት እንደምራመድ ባላውቅም፡ እንዲሁ እራመዳለሁ" ሊል ይችላል። እንዴት እንደሚሆን አናውቅም።

178 እርሱን ለማገልገል ወደ ፊት ሄደች፡ ምክንያቱም የመንፈስ ምሪት… ዘመኑ ያ መሆኑን፡ አብርቶላታል፡ መልእክተኛው እንደሆነ፡ ያ ሊፈውስ የነበረው መሢሕ እንደሆነ፡ ያንንም አመነች። አገልግሎት አስፈልጎት ነበር፡ ያንን ማድረግ እንደምትችል የሚያሳይ ምንም ነገር ሳይኖራት ወደ ፊት ወጣች። በተመራችው ምሪት ብቻ ሄደች። ተመልከቱ! እግዚአብሔር በዓይኖቿ ውስጥ የእንባ እጢዎችን ምንጮች ከፈተ። እርሱን የሰሙት እነዚያው ዓይኖች… እርሱን የሰሙት ጆሮዎቿ፥ ያንን ያዩት ዓይኖች፡ በደስታ ፈሰሱ። ከዚያም ሌላው፡ እግዚአብሔር-የሰጣት ረዥም ፀጉር፡ እነዚያ እንባዎች ወደ ታች ሲፈስሱ። እግዚአብሔር የተዋቡ ፎጣዎችን አቀረበላት (በፀጉሯ)፡ እንዲሁም በእንባዋ። የሕያው እግዚአብሔርን ፍላጎት፡ ፍላጎቶቹን አገለገለች። ስለ እርሱ ሰምታ ነበር፡ አሁን ግን አየችው፡ እርሱን ልታገለግል ቻለች።

179 ኃጢአተኛ ሆይ! አሁን ፍላጎቶቹን ስታይ ለምን እንዲሁ አታደርግም? እርሱ አንተን፡ አገልግሎትህን ይፈልጋልና! በአንድ ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰማኸውን፡ እርሱን አሁን ታየዋለህ። ትናንት ማታ ወደዚህ ሲገባና፡ ያደረገውንም አይተነዋል። ከስብሰባ ስብሰባ፡ እናየዋለን፡ አንዳንዴም እንዲሁ በቅዝቃዜና በግዴለሽነት ተቀምጠን፡ እንዲህ እንላለን፡ "አዎን፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚል አውቃለሁ። ኦህ፡ ሲፈጸም አይ—አይቻለሁ፡ አያችሁ።" ምንም ዓይነት ጉጉት የለንም፡ በትክክል የሚመታንም አይመስልም። የሆነ ነገር ያለ አይመስልም፡ ልክ እያፈሰሳችሁ እንደሆነ...

180 ክብሪትን ወስዳችሁ ስትጭሩት፡ የክብሪቱ ራስ ላይ ሰልፈር በትክክል ከሌለ፡ ሊበራ አይችልም። ደጋግማችሁም ልትጭሩት ትችላላችሁ፡ ነገር ግን የሆነ ኬሚካል እዚያ ላይ ያለውን ሰልፈር ከገደለው፡ አይበራም፡ ምንም ብርሃን አይኖርም። ነገር ግን ያ ኬሚካል፡ ብረት ላይ የሚጫረው ሰልፈር... ሲጫር እዚያ ላይ ካለ፡ ይበራል።

181 የዚህን የመጨረሻ-ቀን መልእክት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ፡ ትክክለኛ ማጽናት ሲኖር፡ የኢየሱስ ክርስቶስንም ሕልውና ስታዩ፡ እርሱ በሕይወቱ ያደረገውን ሰምታችሁ እንደነበር፡ መጽሐፍ ቅዱስም "እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው" ሲል ስትሰሙ፥ የሰዶም ሁኔታ በእግዚአብሔር ቁጣ-ከመንደዱ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል ተመልሶ፡ በሰው ሥጋ ተገልጦ፡ እርሱ ያደረገውን ያንኑ ነገር ሲያደርግ ታያላችሁ። ማይ! ነፍሳችንን ወደ ክብር ሊመታት ይገባል! በውስጣችን የሆነ ነገር ሊያደርግ ይገባል። ለምን? በዚያ ላይ እየተጨመረ ነውና።

182 ሴቲቱ ልብሱን እንዴት እንደነካች፡ እርሱ ምን እንዳደረገ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰምታችኋል። እርሱ ዘወር ብሎ ችግሯ ምን እንደነበር ነገራት፡ እምነቷም አዳናት። አሁን፡ ዓለም ከመቃጠሏ፡ እንዲሁም ዓለም በሰዶም ሁኔታ ውስጥ ከመሆኗ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ ያንኑ ነገር ዳግመኛ እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። አዲስ ኪዳን፡ ነቢዩ፡ የአምላክ-ነቢይ፡ የነቢያት ነቢይ፡ የነቢያት ሁሉ አምላክ፡ የመለኮት ሙላት በሰውነት፡ የእግዚአብሔር... በሥጋ የተገለጠው፡ የዘፍጥረት፡ ፈጣሪ። ሃሌሉያ! የእርሱ ቃል ነው! ይፈጸማል ብሏል! የሰዶምን ሁኔታ እናያለን፡ ዓለምን በዚያ ሁኔታ ውስጥ እናያለን፡ አሁን እርሱ ወርዶ አደርገዋለሁ ያለውን ልክ በትክክል ሲያደርግ እናያለን። አሁን፡ ስለ እርሱ ሰምተናል፡ አሁን እናየዋለን! "በጆሮዎቼ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኖቼ አየሁህ።" አሜን! "በገዛ ዓይኖቼ አየዋለሁ።" እንዴት ያለ ሰዓት ሊሆን ይገባል! እንዴት ያለ ጊዜ ሊሆን ይገባል! የቃሉ ማረጋገጫ! ሁልጊዜ ቃሉ ሲረጋገጥ፡ ያ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ እየተናገረ፡ እናንተ ልታዩት በምትችሉት ሁኔታ ራሱን የሚታይ እያደረገ ነው።

183 አሁን፡ እዚች ከመንገድ የመጣች አንዲት ምስኪን ጋለሞታ አለች፡ በመሠዊያው ላይ፡ በኢየሱስ ፊት ትወድቃለች፡ እግሮቹንም በእንባዋ—በእንባዋ አጠበችው፡ ደግሞም—ደግሞም በፀጉሯ አበሰቻቸው። እግዚአብሔር አከበራት፡ እርሱም፡ "ይህ ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ፡ ይህ ለመታሰቢያዋ ይነገርላት" አለ። ለምን? ምን ያህል ቆሻሻ እንደነበረች ተመልከቱ፡ ነገር ግን የሆነ ነገር ነካት። ከኤደን ገነት ጀምሮ የነበረውን፡ "የሴቲቱ ዘር የእባቡን

ራስ ይቀጠቅጣል፡” የሚለውን፡ የተሰፋውን ቃል አይታለች። ከድንግል የተወለደውን መሢሕ አየች።

184 እርሱ ከድንግል እንደሚወለድ ሰምታ ነበር፡ ዳሩ ግን ያ ሰው በምድር ላይ እንዳለ ሰሙ። የታመሙትን የሚፈውስ አንድ ወጣት ረቢ፡ ነቢይ፡ እንዳለ ሰምታ ነበር። ያንን አመነች! ይኸውም እዚህ በመንገድ ላይ ወረደች፡ እየተራመደች፡ ዙሪያዋን እየተመለከተች። ወደዚያ ማዶ ተመለከተች ያም ታላቅ ግብዣ ሲካሄድ አየች። ሾልካ ወደ አጥሩ ቀረበችና፡ በውስጡ ተመለከተች፡ እርሱም እዚያ ነበር። እዚያ ነበር! የሆነ ነገር፥ “እርሱ ነው” አለ! አያችሁ፡ እንድትነሳሳ ያስፈለጋት ያ ብቻ ነበር። ምን እንደተፈጠረ አያችሁ? የእግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆኖ አየች። በጆሮዋ ሰምታ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኖቿ አየች።

185 አሁን፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ስለ ቤተክርስቲያን ሁኔታ የተሰፋ ቃል እንዳለን ሁሉም ሰው ያውቃል። ቤተክርስቲያንም፡ አሁን ባለችበት ሁኔታ፡ ታላቁን ተልእኮ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በፍጹም ልትፈጽም አትችልም፡ ሙሽራይቱን በፍጹም ልትጠራ አትችልም። የትኛው ያደርገዋል? የጴንጤቆስጤው? በፍጹም አልልም። ሌሎቹም እንዳቸው እያደርጉትም። ያ በስንዴው ላይ ያለው ገለባ ነው። ሲወጣ፡ ልክ እንደ ስንዴው ይመስል ነበር፡ በውስጡ ግን ምንም ስንዴ አልነበረም። እርሱ ሲከፈት፡ ፍሬውም ከዚያ ውስጥ ይወጣል። ተደራጅተው፡ ራሳቸውን ይገድላሉ። መሞቻቸውም እዚያው ነው። አገዳዎች ናቸው። ዳሩ ግን ስንዴው በዚያ በኩል አልፎ ይወጣል፡ አሁንም በሙሽራይቱ-መልክ መገንባት ጀምሯል። በጨለማው ዘመናት ወደ መሬት የወደቀው የስንዴ ቅንጣት፡ መሞት ነበረበት።

186 ተቺው እንዲህ ይላል፡ “መሐሪው አምላክ፡ ቀይ ባሕርን የከፈለ አምላክ፡ እነዚያ ምስኪን ክርስቲያኖች በአንበሶች ሲበሉ፡ ሲቃጠሉና፡ ሁሉም ነገር ሲደርስባቸው ዝም ብሎ እንዴት ያያል? ልክ እንደ ቀልድ፡ ተቀምጦ ይስቃል!” ምስኪን አላዋቂ! “የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ካልወደቀች”፡ የሚለውን አያውቅምን? ልክ እንደ ማንኛውም የስንዴ ቅንጣት ከመሬት በታች ገብቶ እንደሚቀበር ሁሉ፡ እርሱም በመጀመሪያው ተሐድሶ የሉተርን ሁለቱን ቅጠሎች፡ አገዳውን ሊያወጣ፡ በእነዚያ በጨለማ ዘመናት መሞት ነበረበት። ብናኙን፡ አበባውን፡ ያንን ታላቅ የሚሰዮናውያን ዘመን ለማምጣት፡ እዚያ ማዶ በዌስሊዎች ውስጥ፡ መምጣት ነበረበት። የተመረጡትን እንኳ ሊያስት እስኪቃረብ ድረስ፡ ለስጦታዎች መመለስ፡ በጴንጤቆስጤ ውስጥ መምጣት ነበረበት። የስንዴ ቅንጣት ይመስላል፥ ክፈቱት፡ እዚያ ውስጥ ምንም ስንዴ የለም፡ ገለባ ብቻ ነው። ዳሩ ግን ወደዚያ ወደ ኋላ ተመልሰው፡ ያኔ፡ የዋንነስ ድርጅት፡ የሰላሴ ድርጅት፡ ቱነስ ድርጅት፡ ቼርች ኦፍ ጋድ ድርጅት መፍጠር ጀመሩ፡ ሁሉም ተደራጁ፡ ያም በትክክል ሞት ነው! አሁንም ምን ይፈጠራል? ዳሩ ግን ለስንዴው መጠለያ ነው፡ ሁልጊዜም በእርሱ በኩል እያደገ ነበር።

187 አሁን መለየት ጀምሯል፡ ስንዴው መታየት ጀምሯል። ይህ የጴንጤቆስጤ ዘመን አይደለም። ይህ የኋለኛው-ቀን ዘመን ነው። ይህ የሙሽራይቱ ዘመን ነው። ይህ የምሽቱ ብርሃን ነው። የእግዚአብሔርን ንድፍ ለመከተል፡ በሚልክያስ 4 መፈጸም ያለበት ይህ ነው። በሉቃስ 17፥30 ላይ፡ መፈጸም ያለበት ይህ ነው። ይህ ሁለተኛው... እንዲሁም ኤርምያስና፡ የተቀሩት ሁሉ፡

ኢዩኤል ስለዚህ ዘመን የተናገሩት፡ ያ ዘመን **ይህ** ነው። “ሰምቻለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ እየመጣ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አየዋለሁ።”

188 ምንም እንኳን ብዙ… ብዙ ሐሰተኛ አስመሳዮች ቢነሱም፡ እነዚያ ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴ ያደረገውን ሁሉ ለማድረግ በነበራቸው አታላይነት ሁሉ፡ እርሱን ወይም አሮንን በፍጹም አላናወጧቸውም። የት እንደ… ልክ እንደ ኢዮብ፡ መነሳሳታቸው ከማን እንደመጣ ያውቁ ነበር። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እንደሆነ ያውቁ ነበር! ስለ እነርሱ የተናገረው ያው መጽሐፍ ቅዱስም፡ “በመጨረሻው ዘመን አስመሳዮች ይመጣሉ፡” ብሏል። እነዚያ ሃይማኖታዊ የሐይማኖት ተቋማት፡ አንድ ነገር ሲጀመር… መጀመሪያ የጀመረው ማነው? ሙሴ ወይስ እነርሱ? እነርሱ መጀመሪያ ጀምረው ቢሆን ኖሮ፡ ሙሴ አ—አስመሳይ ይሆን ነበር።

189 አሁን እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍቱ እውነት መሆኑን ካጸናው ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ነገር፡ አእምሯችሁን ሊያርቁ የሚሞክሩ ሁሉንም ዓይነት አውጪዎችና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ አግኝተናል። “በጆሯችን ስለ እርሱ ሰምተናል፡ አሁን ግን በዓይናችን እናየዋለን።” አሜን! ታምኑታላችሁን? በሙሉ ልባችን! ምሪት! የሰው ልጅ በሚገለጥበት በዚያ ቀን፡ የሰው ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕዝቡ መካከል ተገለጠ።

190 አንድ ሰው እዚያ ታች በአብርሃምና በቡድኑ ፊት ተራመደ፡ ልክ ተራ-የሚመስል ሰው፡ በልብሱ ላይ አቧራ የነበረው። ጀርባውን ወደ ድንኳኑ አዙሮ፡ “ሚስትህ ሣራ የት ናት፡” አለ? (ሦ-ራ፡ አይደለም፡ ሣራ፥ አ-ብ-ር-ሃ-ም፡ አ-ብ-ራ-ም አይደለም)። ሰሙን ጥርቶ፡ እንዲህ አለው፡ “እሷ የት ናት? ”

191 “ከበስተጀርባህ፡ በድንኳኑ ውስጥ አለች፡” አለው።

192 እንዲህም አለ፡ “የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ እጎበኝሃለሁ” (እሷም በልቧ ሳቀች)። እንዲህም አለ፡ “እሷ ለምን ሳቀች? ” (ኧ-ህ)። አሁን፡ እርሱ ቃል ገብቶ ነበር። የተሰፋውን ልጅ የሚጠብቁት እነዚያ ሰዎች ነበሩ።

193 አሁን፡ ሰዎች በእነዚህ የሐይማኖት ተቋማት ውስጥ “ክርስቶስን እንደሚጠብቁ፡” ምንም ያህል ቢያስመስሉም ግድ አይሰጠኝም፡ ድርጊታቸው ግን እንደማይጠብቁ ያረጋግጣል። ትክክል ነው። ከቃላችሁ ይልቅ ድርጊታችሁ አጥብቆ ይናገራል። የሚያስቡት ሁሉ የሐይማኖት ተቋም አባላትን ስለማፍራት ብቻ ነው፡ ነገር ግን የተወሰኑ ሰዎች፡ **እዚህም እዚያም** አሉ፡ እነዚያም የጌታን መምጣት የሚጠብቁ ናቸው። ሆኖም እነርሱ እየተጠባበቁ ነው… እነርሱም ቢሆኑም። ራሱን የሚገልጠው ለእነርሱ ብቻ ነው፡ የሚረዱትም እነርሱ ብቻ ናቸው።

194 እርሱ ማን እንደነበር የተረዱት የተመረጡት ብቻ ነበሩ። እስቲ አስቡ፡ በምድር ላይ ምናልባት ሦስት ሚሊዮን የሚሆኑ፡ አይሁዳውያን፡ ሰዎች ነበሩ፡ ዳሩ ግን እርሱ መጥቶ እስኪሄድ ድረስ እዚያ እንደነበር ያወቁት አንድ ሦስተኛው እንኳ አልነበሩም። አያችሁ? ነገር ግን ለሚጠብቁት ራሱን ገለጠ፥ ለመጥምቁ ዮሐንስ፡ እ—እንዲሁም በዮሐንስ ለተጠሩት ሐዋርያት፡ እንዲሁም ለመሳስሉት፡ ደግሞም በቤተ መቅደስ ውስጥ ለነበረችው ለዕውሯ ሐና፡ “ክርስቶስን እንደሚያይ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላት ለነበረው” ለካህኑ

ስምዖን ራሱን ገለጠ። እነዚያ ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች፡ የሥነ መለኮት ምሁራንና የመሳሰሉት ሁሉ፡ ሊሆኑ በሚችሉት መጠን ዕውሮች ነበሩ!

195 ዝናብ ዘሩን ሊያበቅል የሚችለው፡ ዘሩ አስቀድሞ እዚያ ካለ ብቻ ነው። በመጀመሪያ በአባታችሁ ውስጥ ዘር እንደነበራችሁ፡ እርሱም እንዳላወቃችሁ፡ ሆኖም በአባታችሁ ውስጥ እንደነበራችሁ ሁሉ ነው። ነገር ግን በእናታችሁ ማሕፀን በኩል፡ በእርሱ አምሳል ተገለጣችሁ፡ ከዚያም ሊያነጋግራችሁ ቻለ። እግዚአብሔር፡ ታላቁ እግዚአብሔር፥ የዘላለም ሕይወት ካላችሁ፡ የዘላለም ሕይወት ዘር በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ውስጥ ነበር። እናንተም እዚያ ነበራችሁ፡ በእርሱ አሳብ ውስጥ ነበራችሁ፡ ስማችሁና ሁሉም ነገር። እርሱም፡ አስቀድሞ በማወቅ ዕውቀቱ፡ ይህን እንድታዩ ወሰናችሁ። ያልተወሰናችሁት ደግሞ፡ ይህን በፍጹም አታዩትም። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ "ዘመኑ ደርሷል!" አታምኑትምን? ሕይወታችሁን ለእርሱ ስጡ። ማቆም አለብኝ፡ ከዘጠኝ ሰዓት አልፏል።

ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

196 "ጌታ ሆይ፡ ስለ አንተ፡ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ!" ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እነዚህን ሰዎች እየጠበቁ ሳሉ ባርካቸው።

197 አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ ነው። መንፈስ ቅዱስ (እንደሚያደርገው አምናለሁ) አእምሯችሁን እንዲመረምር፡ እንዲፈትናችሁ፡ ነፍሳችሁን እንዲፈትንና፡ በእውነት ታምኑ እንደሆነ እንዲያይ አደርጋለሁ። ዳሩ ግን እዚያ ውስጥ ትንሽ ጥርጣሬ ካገኛችሁ፡ እጃችሁን ታነሳላችሁን? እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ልይህ። ስለ አንተ ሰምቻለሁ፡ ዳሩ ግን በእውነት አይቼህ አላውቅም። ልይህና፡ አምናለሁ።" መልካም። ያ ጥሩ ነው።

198 እርሱን እንደ አዳኛችሁ የማታውቁት እዚህ አላችሁን? እጃችሁን አንሱና፡ እንዲህ በሉ፡ "እኔ... እ—እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፡ ነገር ግን እኔ... እ—አንተ እንዳይህ ብቻ ከፈቀድክልኝ፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እነርሱ የሚናገሩትን ይህን ቃል ግለጥ። ኢዮብ ያየህ በዚህ መንገድ እንደሆነ አውቃለሁ። አብርሃም ያየህ በዚህ መንገድ እንደሆነ አውቃለሁ። የተቀሩት ሁሉ ያዩህ በዚህ መንገድ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ምክንያቱም የጸናው የተሰፋ ቃልህ ነበርና። እኔም ሁሉንም ዓይነት ነገሮች፡ አታላይ ዘዴዎችንና፡ ሁሉንም ነገር ሰምቻለሁ፡ ነገር ግን በ1933 በወንዙ ዳር በመልአክ የተነገረ፡ የመጨረሻ-ዘመን መልእክት፡ በምድሪቱ እንዳለ ተረድቻለሁ። የፈውስ አገልግሎቶች ሲካሄዱ ሰምቻለሁ፡ ያ ሲሆንም፡ በዚያው ያረጀ የየሐይማኖት ተቋም ዐዘቅት ውስጥ ሊቆይ እንደማይችል አውቃለሁ።" ለዚያ አልተላከም፡ እዚያም ቆይቶ አያውቅም። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ?...

199 ሙሴ መጥቶ፡ "ኖኅ እንዳደረገው መርከብ እንሥራና፡ ከግብፅ ወጥተን በወንዙ ላይ እንንሳፈፍ" ብሎ ቢሆን ኖሮ፡ ምን ይሆን ነበር? ኦህ፡ አይሆንም። አያችሁ? አይሆንም! ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክት ነበረው፡ መገለጡም እርሱ ነበር። ያ ነቢይ በቦታው ላይ መነሳቱ፡ ልክ እዚያው ለእስራኤል ማረጋገጥ ነበረበት። ለአራት መቶ ዓመታት ነቢይ አልነበራቸውም፡ ነቢይ አልነበራቸውም፡ አሁን እዚህ አንድ ነቢይ በሁኔታው ላይ ተነሳ። እነርሱም የሆነ ነገር ሊፈጠር እንደሆነ ማወቅ ነበረባቸው።

200 እስራኤል ዳግመኛ ለመቶዎች ዓመታት ነቢይ አልነበራቸውም፡ እነሆ ኢየሱስ በሁኔታው ላይ መጣ። በውኃ ጉድጓዱም አጠገብ የነበረችው ሴት፡ እንዲህ አለች፡ "ጌታዬ፡ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። አሁን፡ ለአራት መቶ ዓመታት አንድም አልነበረንም" አለች። ምክንያቱም፡ በልቧ ውስጥ የነበረውን አውቆ ነበርና። አያችሁ?

201 አሁን፡ በተሃድሶ አራማጆች አማካይነት የቤተክርስቲያን ዘመን እንደሚመጣ ተስፋ ተሰጥቶናል፡ ተቀብለናቸዋል። ነገር ግን፡ እርሱ በምልክያስ 4፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት ንድፉን እንደሚጠብቅ፡ ምን እንደሚፈጠር፡ "የልጆችን ልብ ወደ ሐዋርያት አባቶች እምነት ለመመለስ" ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ለዚያው ዓላማ! ቤተክርስቲያንም በየሐይማኖት ተቋማትና በኢዝሞች በጣም ተከፋፍላለች፡ እስክትሞትም ድረስ ተበጣጥሳለች፥ ተሸካሚ ብቻ ነበረች። ከዚያም በሰባተኛው መልአክ መልእክት ዘመን፡ ሰባቱ ማኅተሞች እንደሚገለጡ፡ እንዲሁም ሰባተኛው መልአክ፥ መልእክቱን ማሰማት ሲጀምር (ራእይ 10) የእግዚአብሔር ምስጢራት እንደሚታወጁ ተስፋ ሰጥቷል፡ ያም የፈውስ አገልግሎቱ ሳይሆን፡ የፈውስ አገልግሎቱን የሚከተለው መልእክት ነው።

202 ኢየሱስ የታመሙትን መፈወስ እስከቻለ ድረስ "ታላቅ ሰው" ነበር። ነገር ግን፡ "እኔና አብ አንድ ነን" ባለ ጊዜ።

203 "ኧ-ኧ! ያ ስህተት ነበር!"

204 ኢዮብ የሆነ ነገር እስኪደርስበት ድረስ፡ "ታላቅ" ነበር። አያችሁ? ሁልጊዜም የሚሆነው እንደዚሁ ነው።

205 እመኑ! አሁን ትቀበሉታላችሁን? እጃችሁን አንሱና፡ "በእርግጥ አምነዋለሁ። ልቀበለው እፈልጋለሁ፡" በሉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ያ መልካም ነው።

አሁን ጸጥ ብላችሁ ተቀመጡና ለአፍታ ጸልዩ።

206 ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ በከበረው ጊዜ፡ አንድ ቀን በእርግጥ የነጎድጓድ ድምፅ የሚኖርበት የእግዚአብሔር ልጅም በጩኸት፡ በመላእክት አለቃ ድምፅና፡ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማያት የሚወርድበት፡ በክርስቶስ የሞቱትም የሚነሱበት፡ ልክ እንደዚህ ያለ ጊዜ ይሆናል። አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ እያንዳንዳችን ለምንሰጠው ቃል ሁሉ፡ ለምንናገረውም ቃል ሁሉ መልስ መስጠት እንዳለብን እናውቃለን፡ እንገነዘባለንም። በልባችን ውስጥ ላሉት አሳቦች እንኳን፡ መልስ እንሰጥባቸዋለን። አምላክ ሆይ፡ እዚህ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ልብ እንድታነጻ፡ በኢየሱስ ስም፡ እጸልይሃለሁ። ልቤን አንጻ፡ የዚህን ሕዝብ ልብ አንጻ። ጌታ ሆይ፡ ዝግጁዎች እንድንሆን፡ ዛሬ ማታም የሁሉን ቻይ አምላክን ክብር ለማየት መንፈሳዊ ዓይኖቻችን እንዲከፈቱ አድርግ። ስለ እርሱ ሰምተናል፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ እንድናየው እንድትፈቅድልን እንጸልያለን። አባት ሆይ፡ ይሁንልን። እነዚህን በረከቶች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትሰጠን እጸልያለሁ። አሜን።

207 አስታውሱ፥ በተቀመጣችሁበት ቦታ፡ በልባችሁ ውስጥ፡ ትንሿን መሠዊያችሁን አዘጋጁ። እንዲህም በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን ወደ

ልቤ ግባ። የሆነ ነገር... አጥብቄ ልይዘው የምችለውን የሆነ ነገር ስጠኝ። ‘እዚህ እንዳለህ’ የሚነግረኝን ያ ምሪት እንድሰማኝ አድርግ።”

208 አሁን፡ ለሰዎች ለመናገር እንዴት ያለ ንግግር ነው! ለማድረግ እንዴት ያለ—ያለ ነገር ነው! አሁን ጌታ እግዚአብሔርን ልጠይቅ ነው፡ ልጠይቅ...

209 ስንቶቻችሁ ናችሁ ቴፖቹን የምትወስዱት? **ጌቶች ሆይ፡ ሰዓቱ ስንት ነው?** የሚለውን ሰምታችኋል፥ ነገሩ ከመፈጠሩ ከአንድ ዓመት በፊት፡ እነዚያን መጽሔቶችና ነገሮች አላሳየንምን? ሳይንስ በዚህ ጉዳይ ግራ ተጋብቷል። ጌታ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ በራዕይ 1 ላይ እንዲሁም በዳንኤል እንደምታዩት፡ በዚያ ነጭ ዊግ ዘውድ ለብሶ፡ የሰማይ እና የምድር ሉአላዊ ዳኛ ሆኖ ነበር። በዚያ፡ የሳይንስ ሰዎች ራሳቸው እንኳ ሊያዩት በማይችሉበት ጊዜ። እዚያ ውጪ በአሪዞና ዩኒቨርሲቲ ባለው የጠፈር ምርምር ጣቢያና፡ እዚያ ታች በሜክሲኮ በኩል፡ እየፈለጉ ነው፡ ላለፉት ሁለት ዓመታትም ሲፈልጉ ቆይተዋል። እዚያም “ሊከሰት እንደሆነ፡” አስቀድሞ፡ ተነግሯችሁ ነበር።

210 ስለ አላስካው የመሬት መንቀጥቀጥስ ምን ትላላችሁ? ሆሊውድ ወደ ባሕር ውስጥ ስትወድቅ ተመልከቱ! የማይሆን ከሆነ ጠብቃችሁ እዩ። እርሱ እስካሁን ድረስ የተሳሳተ ነገር ነግሮኝ አያውቅም፡ ያደርገዋል። አያችሁ? በታሪክ የመጨረሻ ሰዓታት ውስጥ እየኖርን መሆን አለመሆናችንን ዝም ብላችሁ ተመልከቱና እዩ። በምን ሰዓት እንደሚመጣ ማንም አያውቅም። ዳሩ ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፥ በአሁኑ ሁኔታዬ፡ ጤነኛ አእምሮ ካለኝ፡ እንዲሁም ክርስቲያን ባልሆን ኖሮ፡ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን ለመሆን በእርግጥ እፈልግ ነበር፡ እንጂ የየሐይማኖት ተቋም አባል መሆንን አይደለም። ስለጮኽኋችሁ ብቻ በዚህ ላይ አትደገፉ። ዛሬ ጠዋት ያንን ሰምተናል፡ በእግዚአብሔር ቃልም አረጋግጠነዋል፥ ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ነው፡ ሞትን ከማስከተል በቀር ምንም አላደረገም። በአገዳው ውስጥ አትሁኑ፡ በሕይወቱ ውስጥ ሁኑ። አያችሁ? በእግዚአብሔር እመኑ።

211 ይህን የተስፋ ቃል የሰጠው ያ አምላክ፡ በዘፍጥረት መጽሐፍ፡ ራሱን እንደገለጠ፡ ለአብርሃምም ተገልጦ ያንን ተአምር ያደረገው እርሱ እንደሆነ ታምናላችሁ... ያው እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ፡ የሰው ሥጋ ሆኖ፡ ከድንግል ተወለደ። በእርግጥ፡ ያኛው ቲዮፋኒ ነበር፡ ዳሩ ግን በሰው ሥጋ በመጣ ጊዜ ያው ሰው ነበረ፡ ያንኑ ነገርም ያደርግ ነበር፡... እግዚአብሔር በምልክያስ 4 መሠረት ሊያደርግ ቃል የገባለትን፡ በእርሱ በኩል ሊናገር የሚችልበትን፡ መተላለፊያ የሆነ ሰው ማግኘት ቢችል ኖሮ፡ እዚያ አደርገዋለሁ ያለውን ያንኑ ነገር ያደርጋል ብላችሁ አታምኑምን? ያንን ታምናላችሁን? እንደሚያደርግም፡ እኔ አምናለሁ።

212 ልብሱን ለመንካት የእርሱ እምነት፡ ልብሱን ለመንካት እምነቱ ሊኖራችሁ እንደሚችል ታምናላችሁን? አሁን ልብሱን ለመንካት እምነት እንዳላችሁ የሚነግራችሁ የሆነ ነገር በልባችሁ እየተናገረ መሆኑን ታምናላችሁን? ያንን ማድረግ እንደምትችሉ ታምናላችሁን? እንግዲያውስ ዘርግታችሁ በእምነታችሁ ንኩት፡ በስሜት ሳይሆን፡ ፍጹም ንጹሕ በሆነ፡ ባልተበረዘ እምነት ብቻ። እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ። በሙሉ ልቤ አምናለሁ። እንድትነካኝ እፈልጋለሁ ምክንያቱም አንተ—አንተ ስታደርገው ሰምቻለሁ፡ አሁን ግን በገዛ ዓይኖቼ ላየው እፈልጋለሁ” በሉ።

213 እኔ ልነካችሁ አልችልም። ሊነካችሁ የሚችለው እግዚአብሔር ነው። ያደርገዋል ብላችሁ ታምናላችሁን?

214 ልክ እዚህ ወደ ግራዬ ወደ ኋላ እየተመለከትኩ ነው። እንደተናገርኩት፡ ወደዚያ የሚሰብ፡ የሆነ መተላለፊያ ያለ፡ ይመስላል። ወደዚያ አቅጣጫ ስለመራሁት፡ አሁን በሚያስደንቅ ሁኔታ እየመጣ ነው። ከባሏ ጋር እዚያ የተቀመጠች አንዲት ሴት ናት። ከዚህ አይደለችም። የመጣችው ከቴክሳስ፡ ዳላስ ነው። እየተሰቃየች ነው፡ ባሏም እንዲሁ እየተሰቃየ ነው። በተወሳሰበ በሽታ እየተሰቃየች ነው፡ ቀዶ ጥገናም አድርጋ ነበር። ትክክል ነው። ባሏም በጀርባው ላይ በሆነ ነገር፡ በጀርባ ሕመም ይሰቃያል። ሚስተርና ሚሰስ ኮርቤት፡ ከቴክሳስ፥ ዳላስ፡ ቴክሳስ። እንደዚያ ከሆነ፡ እጃችሁን አንሱ። ለእናንተ እንግዳ ነኝ። ትክክል ነውን? ያንን የማውቅበት ምንም ዓይነት መንገድ በዚህ ዓለም የለም። ምንድን ነው? "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን አየሁህ።" ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? አሁን ያንን ባልና ሚስት ጠይቁ። በሕይወቴ አይቻቸው አላውቅም። "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አየሁህ።"

215 ማመን ከቻላችሁ፡ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሊያቀርብላችሁ ይችላል።

216 እዚያ እጁን አገጩ ላይ አድርጎ የተቀመጠው ያ ሰው፡ ከፍተኛ የደም ግፊት ያለበት። እግዚአብሔር እንደሚፈውስህ ታምናለህ፡ ወዳጄ? ታምናለህ? እጅህን **እንደዚህ** አድርገህ ተቀምጠህ፡ እግዚአብሔር ከዚያ ከፍተኛ የደም ግፊትህ እንደሚፈውስህ ታምናለህን? ያንን የምታምን ከሆነ፡ እጅህን አንሳ። መልካም፡ ያደርገዋል። በሕይወቴ ያንን ሰው አይቼው አላውቅም፡ ስለ እርሱ ምንም አላውቅም። ነገር ግን ኢየሱስ፡ እዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ ሲናገር ሰምታችኋል፡ አሁን ታዩታላችሁ! ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? "ብታምኑ፡ ሁሉ ይቻላል።" ለሚያምኑት ብቻ! ያንን ለማድረግ እውነተኛ፡ ንጹሕ እምነት ይጠይቃል። ነገር ግን ማመን ከቻላችሁ፡ እግዚአብሔር ያደርግላችኋል።

217 እዚያ ጀርባ የተቀመጠች፡ እኔን የምትመለከት፡ ጉሮሮዋ ላይ እንቅርት ያለባት አንዲት ሴት አለች።

218 በአጠገቧ የተቀመጠችው፡ በአጠገቧ የተቀመጠችው ሴት፡ ግልጽ እንዲሆንላት፡ እዚያ ያለችው ያቺ ሴትም እንዲሁ፡ ከፍተኛ የደም ግፊት አለባት። ትክክል ነው።

219 በአጠገቧ የተቀመጠችው ሴት፡ እሷም፡ የ—የሆነ ችግር አለባት። እሷም ከዚህ አይደለችም፡ ከአርካንሳስ ናት። እያመለጣቸው ነው። ሚስ ፊሊፕስ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኚና ተፈወሺ! ታምኚዋለሽን? በሙሉ ልብሽ? ትቀበይዋለሽን? በትክክል። እንግዲያውስ ልታገኚው ትችያለሽ።

አሁን እናንተ፡ "ያ ምስጢራዊ ነው" ትላላችሁ። አይ! አይ!

220 ኢየሱስ፡ "ስምህ ስምዖን ነው፡ አንተ የዮና ልጅ ነህ" አለ። ልክ ነውን?

221 "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አየሁህ።" አሁን ምን እንደተፈጠረ አታዩምን? አንድ ሰው ዝም ብሎ እዚያ ተቀምጦ፡ እያየ፡ እያመነ፡

እየታመነ ሳለ፡ ድንገት እዚያው ይፈጠራል። አያችሁ?

222 ልጄ፡ ዛሬ ማታ፡ ከትናንት ማታው በተሻለ፡ ጥሩ ስሜት ይሰማሃልን? ተረጋግተሃልን? አሁን ሁሉም ነገር ደህና ነው፡ ልትፈወስ ነው (ኧ-ህ)። ትናንት ማታ እዚህ ተቀምጦ፡ ጭንቅላቱን ያጋጭና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ያደርግ ነበር፥ አሁን፡ ዛሬ ማታ ግን፡ ጨዋ ሰው ይመስላል። አያችሁ? ስለ ነገሮች ትንሽ ግራ ተጋብቶ ነበር፡ ዳሩ ግን አሁን ሁሉም ነገር ተስተካክሏል። አያችሁ? ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል። አያችሁ? "በዚያም ቀን፡ የሰው ልጅ ይገለጣል፡ አያችሁ፡ ሰዶም ከመቃጠሏ ጥቂት ቀደም ብሎ።"

223 "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አየሁህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን ቃል ሲገባ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ያ የተሰፋ ቃል ሕያው ሆኖ አየዋለሁ።" አያችሁ? "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አየዋለሁ።" ያ እርሱ መሆኑን ስንቶቻችሁ ታምናላችሁ? (ኦ እግዚአብሔር ሆይ!)

224 አሁን፡ እዚህ ሳለን... እየመሸ ነው። ነገ ማታ ታላቅ የፈውስ አገልግሎት ይኖረናል። እኔና ወንድም ሙር እዚህ ቆመን በሰልፉ ውስጥ ማለፍ ለሚፈልግ እያንዳንዱ ሰው እንጸልያለን ብለን እየጠበቅን ነው። ዳሩ ግን ዛሬ ማታ ይህን ስናገር፡ የመሠዊያ ጥሪ ብቻ አደርጋለሁ ብዬ አስቤ ነበር። ነገር ግን ከዚያ፡ "አይ" ብዬ አሰብኩ፡ እዚያ ላይ፡ "በጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኔ አንተን ማየት እፈልጋለሁ" ብሏልና። አሁን እርሱ እዚህ አለ። ያንን ታምናላችሁን?

225 አሁን እርስ በርሳችን እጃችንን እንጫጫን። አሁን፡ አስታውሱ፡ **ይህን** እንደሚያደርግ ቃል የገባው ያው አንዱ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡" ብሏል። ያንን ብሏልን? አማኞች ናችሁን? "አሜን፡" በሉ። እንግዲያውስ፡ ልክ አሁን፡ ሲፈጽመው የምታዩትን ይህን የተሰፋ ቃል የሰጠው ያው እግዚአብሔር፡... ከእነዚያ ሰዎች ማንኛውንም ጠይቁ፡ አይቻቸው አላውቅም፡ ስለ እነርሱም ምንም አላውቅም። አሁንም ቢሆን አላውቃቸውም፡ አያችሁ፡ ለእኔ የማይቻል ነው። ነገር ግን ያ ቃል መፈጸም አለበት! እንግዲህ፡ ያ ከተፈጸመ፡ እኛ በመጨረሻዎቹ ዘመናት ውስጥ እንዳለን ያሳያል፡ የሰው ልጅ ሊሆን... ሊመጣ ዝግጁ መሆኑን እናውቃለን፡ ምክንያቱም እርሱ በሰው ሥጋ ራሱን እየገለጠ ነውና። ትክክል ነውን?

226 እንግዲያውስ እውነት መሆኑን እናውቃለን፡ በእርሱም አማኝ መሆናችሁን ትናገራላችሁ፡ እርስ በርሳችሁም እጃችሁን ተጫጭናችኋል። እርስ በርሳችሁም እጃችሁን ከተጫጫናችሁ፡ **ይህን** በዓይኖቻችሁ ፊት እውነት ለማድረግ እዚህ ያለው ያው የእግዚአብሔር ልጅ፡ ያው ልጅ፡ "ይድናሉ" ለማለት እዚህ አለ! ያው የእግዚአብሔር ልጅ! "'አማኞች እጃቸውን ቢጭኑ፡ ይድናሉ' ማለቱን፡ ሰምቻለሁ። በጆሮዎቼ ሰምቻለሁ፡ አሁን በዓይኖቼ ልየው። እርሱ እንደሚያደርገው ቃል ገብቷልና።"

አሁን ስጸልይ፡ እናንተም ጸልዩ።

227 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በሰማይ አምላክ ጌታ ሰም፡ መንፈስህ በእነዚህ ሰዎች ልብ ውስጥ ይውረድ፥ ይህን የተሰፋ ቃል ለእነርሱ የሚያረጋግጥላቸው፡ ያው ከእግዚአብሔር የሆነ እውነተኛ እምነት። እርስ በርሳቸው እጃቸውን በመጫን

ትእዛዛትህን ሲታዘዙ፡ የሰማይ አምላክ እያንዳንዳቸውን ይፈውሳቸው። ጌታ ሆይ፡ እንዲሁ ይሁን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለክብርህ ሲባል፡ እንዲሁ እንዲሆን ፍቀድ።

228 አሁን፡ የጠየቃችሁትን እንዳገኛችሁ ታምናላችሁን? በልባችሁ ውስጥ የሆነ ነገር ይነግራችኋልን? "እንግዲህ፡ አብቅቷል! ተፈጽሟል!" የሚለው፡ ያ ትንሽ የምሪት ብልጭታ፡ ይሰማችኋልን?

229 የእግዚአብሔር ትእዛዝ በጆሯችን ልንሰማው እንደምንችል ተናግሯል፡ አሁን በዓይናችን ልናየው እንችላለን። ኢዮብ፡ "በጆሮ መስማት ስለ አንተ ሰምቼ ነበር፡ አሁን ግን በዓይኖቼ አየሁህ" ብሏል።

230 አሁን፡ በቃሉ ሰምታችሁታል፡ ቃሉን በመስማት፡ "እምነት ከመስማት ነው፡ መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።" አሁን በተግባር ሲውል፡ በዓይኖቻችሁ ታዩታላችሁ! አሁን፡ ያንን የተናገረው ያው አምላክ፡ እነዚህ ነገሮች በሚፈጸሙበት ጊዜ፡ "ይህን የሚያምኑ በታመሙት ላይ እጃቸውን ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ" ያለው አምላክ ራሱ ነው። አሁን "እንደ ተፈወሳችሁ" በልባችሁ ውስጥ ገብቷልን? ከገባ እጃችሁን አንሱ። አሜን! ያ እውነተኛ ሐዋርያዊ ፈውስ ነው። በእውነት ነው የምትሉት? በሙሉ ልባችሁ ታምኑታላችሁን? ሃሌሉያ! የሚያስፈልገን ያ ብቻ ነው።

እንግዲያውስ፡ በእግራችን እንቁምና ምስጋና እንስጠው።

231 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እናመሰግንሃለን። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን።

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
ሰዎች ሆይ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ እድፍን ሁሉ አሰወግዷልና።

232 አሁን፡ ትወዱታላችሁ? አሁን ሁላችንም፡ በአንድነት፡ እናንተ ሰዎች ሁሉ፡ ክብርን እንስጠው። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ያ በእግዚአብሔር ከተገለጠላችሁ፡ በዳናችሁበት መንገድ፡ "እንደዳናችሁ" በነገራችሁ በዚያው መንገድ፡ ልክ በኢዮብና በነቢያት እንዳደረገው፡ እግዚአብሔር በተንቀሳቀሰበት በዚያው መንገድ፡ እንደ ክርስቲያን በዚያ መንገድ በእናንተ ውስጥ ተንቀሳቅሷል፡ "እንደተፈወሳችሁ" በመለኮታዊ መገለጡ አሳይቶአችኋል፡ እንግዲያውስ ያ እንዳይሆን የሚያግደው ምንም ነገር የለም።

ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሁሉ ክብርን እንስጠዋለን፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ... (ጥርጣሬን ሁሉ፥ ጥርጣሬን ሁሉ
አሰወግዷልና።)

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፥
ሰዎች ሆይ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ እድፍን ሁሉ አሰወግዷልና።

233 ኦህ፡ አትወዱትምን? አህ፡ እንዴት ድንቅ ነው። "ጌታ ሆይ፡ በጆሮዬ፡ ስለ አንተ ሰምቻለሁ፡ እምነትም ከመስማት ይመጣል፥ ዳሩ ግን አሁን አይሃለሁ፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዳደረገው በሕዝቡ መካከል ራሱን

ሲያሳውቅ፡ ዓለም በሰዶም ሁኔታ ውስጥ በምትሆንበት ዘመን የሰው ልጅ ራሱን እንደሚገልጥ በገባው ተስፋ እዚህ ታይቷል።"

234 ሦስት መልእክተኞችም ወጡ፡ ከሰማይም ወረዱ።

235 በሰዶምም ውስጥ የየሐይማኖት ተቋም ቡድን ነበረ፡ ቢሊ ግራሃምና ኦራል ሮበርትስም ወደዚያ ወረዱ። እንደነገርኳችሁም አስታውሱ፡ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የትም ሰፍራ ስሙ እንደ አብርሃም፡ ሃ-ም በሚል የሚጠናቀቅ፡ ለቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ መልእክተኛ፡ እስከ አሁን ድረስ ተልኮ አያውቅም። G-r-a-h-a-m፡ ስድስት ፊደላት፡ ለዓለም፡ የሰው ቁጥር ነው።

236 ዳሩ ግን አብርሃም በስሙ ውስጥ ሰባት ፊደላት ነበሩት፡ የእግዚአብሔር ሙሉና ፍጹም ቁጥር። አያችሁ?

237 ወደዚያም የገቡት መልእክተኞች ምን እንዳደረጉ ልብ በሉ፥ ቃሉን ሰበኩ፡ ጠርተው አወጧቸው፡ ንስሐም እንዲገቡ ነገሯቸው።

238 ዳሩ ግን ከአብርሃም ጋር ወደ ኋላ የቀረው፡ አያችሁ፡ ከኋላው ባለው ድንኳን ውስጥ ሣራ ምን እያደረገችና ምን እያሰበች እንደነበረ ለአብርሃም በመንገር ተአምር አደረገ። በዚህም አካል ውስጥ የነበረው፡ ኢየሱስ፡ "ዓለም እንደዚያን ጊዜው፡ በሰዶም ሁኔታ ውስጥ ስትሆን፡ የሰው ልጅ ዳግመኛ ይገለጣል፡" አለ። ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችም ሁሉ ይህ እውነት መሆኑን ያጸናሉ። የ... "በመጀመሪያ" [ጉባኤው፡ "ቃል ነበረ" አለ፡—እርታዒ።] "ቃልም በ" ["እግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡"] "ቃልም" ["እግዚአብሔር ነበረ።"] "ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" ልክ ነው? አሁን ያንኑ ተሰፋ የተሰጠበትን፡ የሉቃስን፡ የሚልክያስን ቃል፡ ዛሬ ያሉትን እነዚህን ሌሎች ተሰፋዎች ሁሉ፡ ሥጋ ሆኖ፡ በእኛም መካከል አድሮ፡ በጆሮቻችን የሰማነውን እናያለን፥ አሁን በገዛ ዓይኖቻችን የእርሱን ቃል ራሱ ሲተረጉመው እናየዋለን፡ የማንም ሰው ትርጓሜ አያስፈልገንም። የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሆይ፡ እዚህም በሰልክም ያላችሁ፡ ጊዜው ሳይረፍድ፡ ቶሎ ንቁ! እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

> እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
> ቀድሞ ስለወደደኝ
> መዳኔንም ገዛ
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

239 ማሰብ ትችላላችሁን፡ ቤተክርስቲያን፥ በገዛ ዓይኖቻችሁ እያያችሁ መሆኑን... ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ሲገለጥ፡ የዘመኑ ተሰፋ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ ሕያው ቃል በተፈጥሮአዊ መልክ ሲተረጎም በገዛ ዓይኖቻችሁ እያያችሁ፡ እግዚአብሔር በእኛ መካከል ነው! "በገዛ ዓይኖቼ አየዋለሁ፡ ያንን... እርሱ እንደሚያደርገው ሰምቻለሁ።" የቀድሞ፡ ጠቢባን ሁሉ ይህንን ቀን ተጠባበቁ፡ አሁን በገዛ ዓይኖቻችን ሲገለጥ እናየዋለን። ሰንቶች ጯኺዎቹ የቀድሞ ሜቶዲስቶች፡ ባብቲስቶች፡ እና እውነተኛ፡ ትክክለኛ ጴንጤቆስጤዎች በዘመናቸው፡ ይህ ሲሆን ለማየት ናፈቁ! ብዙዎቹ እንደሚሆን ያውቁ ነበር። ዳሩ ግን እኛ ዛሬ ማታ ይህ ሲሆን እያየን ቆመናል! ኦህ! አትወዱትምን?

240 አሁን፡ ኢየሱስ፡ “እርስ በርሳችሁ ስትዋደዱ፡ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ” አለ። ስለዚህ እርሱን እንደምንወደው ሁሉ፡ እርስ በርሳችን እንጨባበጥና **አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ** ብለን እንዘምር፡ መልካም።

> አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
> አቤት፡ ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
> ክብርን ሁሉ ስጡት... (እንዴት ነህ? )... ሰዎች፡
> ደሙ እድፍን ሁሉ አሰወግዷልና።

241 በዚያች ሌሊት የብልጣሶር ንግሥት በንጉሥዋ ፊት ምን አለች? “በመንግሥትህ ውስጥ ጥርጣሬዎችን የሚፈታ ሰው አለ።” መንፈስ ቅዱስም፡ ዛሬ ማታ፡ ጥርጣሬዎችን የሚፈታ ነው! ያንን ታምናላችሁን? (ምን ፈለገች? ኡህ፡ ችግር የለውም።) ጥርጣሬዎችን የሚፈታ! አሁን፡ የክርስቶስ ደም እድፍን ሁሉ ያሰወግዳል፡ የጥርጣሬን እድፍ። በዓለም ላይ ካለማመን የሚበልጥ ኃጢአት የለም፡ “በማያምን ላይ ግን፡ አሁን ተፈርዶበታልና!” ልክ ነው? “የማያምን ተፈርዶበታል።” አንድ ኃጢአት ብቻ ነው ያለው፡ እርሱም አለማመን ነው። ማጨስ ኃጢአት አይደለም፡ መርገም ኃጢአት አይደለም፡ ማመንዘር ኃጢአት አይደለም፡ መዋሸት ኃጢአት አይደለም፥ ያ ኃጢአት አይደለም፡ ያ ያለማመን ውጤት ነው። አለማመን! ያንን የምታደርጉት ስለማታምኑ ነው። የምታምኑት ከሆነ፡ ያንን አታደርጉትም።

242 ኡህ! ኡህ! ምን... ድንቅ ነው! የበጉም ደም ጥርጣሬን ሁሉ አጥቧል። ቃሉን፡ አጥብቀን እናምናለን። ቃል ሥጋ እንደሆነ እናምናለን። አሁንም ቃሉን ለማጽናት ሳልዋቱ በመረጋገጡ ቃል ሥጋ **እንደሆነ** እናምናለን። ታምኑታላችሁን? እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

243 በጌታ ፊት ታላቅ ጊዜ ለማሳለፍ፡ ጠዋት እዚህ እንደምናያችሁ ተስፋ እናደርጋለን። አሁን አንገታችሁን ዝቅ አድርጉ፡ አገልግሎቱን ለወንድም ሊንድሴይ እሰጣለሁ።

65-1127E መስማትን ሰምቼ ነበር አሁን ግን አየሁ
ላይፍ ተበርናክል
ሽሬቭፖርት, ሉዊዚያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፦

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org